ይህም ፡ መደረጉ ፡ የጠላት ፡ መርከብ ፡ ለማስጠም ፡ እንዳይችል ፡ ነው ። የመ
ጨረሻው ፡ ደርብ ፡ ለመዘዋወርያ ፡ የሚችል ፡ ግንብ ፡ ዙሪያውን ፡ ተሠርቶበታል ።
ወታደሮች ፡ በዚህ ፡ ላይ ፡ ቁመው ፡ መሣሪያ ፡ ሊወረውሩ ፡ ይችላሉ ።
፫ ፤ የሮማውያን ፡ የንግድ ፡ መርከቦች ፡ እነርሱ ፡ እንደሚፈልጉዋቸው ፡ ሁነው ፡ የተ
ሠሩ ፡ ናቸው ። ቀድሞ ፡ የባሕርን ፡ መንገድ ፡ የሚያመለክት ፡ ማግኔት ፡ ሳይ
ገኝ ፡ መርከቦች ፡ መተላለፊያ ፡ በሌለው ፡ ማዕበል ፡ ላይ ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ ለመዞ
ራት ፡ ይችላሉ ። በባሕር ፡ ላይ ፡ መሄድም ፡ እንደሚያስፈልግ ፡ ሆኖ ፡ ወደ ፡ ጠ
ረፍ ፡ እንዲሆን ፡ ተወሰነ ። አምሳ ፡ ቶን ፡ የሚሸከሙ ፡ መርከቦች ፡ የሆኑ ፡ እን
ደ ፡ ሆነ ፡ ዋጋ ፡ ያላቸው ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ሰፊ ፡ ይባላሉ ።
፬ ፤ ሮም ፡ ቀድሞ ፡ ከሜዴቴራኒያን ፡ መንግሥቶች ፡ በንግድ ፡ መርከቦች ፡ ከምሥራቅ ፡
ብዙ ፡ ነገር ፡ ታገኝ ፡ ነበር ። አውግስጦስ ፡ ምስርን ፡ ድል ፡ እስኪያደርግ ፡ ንግዱ ፡
ፈጽሞ ፡ የርስዋ ፡ ነበር ። እስክድርያም ፡ በዚህ ፡ ንግድ ፡ መኻከል ፡ ነበረች ።
፭ ፤ ከህንድ ፡ ወደ ፡ ኢጣሊያ ፡ ገቢ ፡ ንግድ ፡ ቅመምና ፡ መድኀኒት ፡ ነበር ። የጥጥ ፡
ልብስና ፡ ግምጃ ፡ ከኮርማንድልና ፡ ከማለባር ፡ ሐር ፤ ከቺን ፡ ዕንቍና ፡ ሌላም ፡
የከበረ ፡ ደንጊያ ፡ ከቤንጋል ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ የሆነውን ፡ ሥጋጃና ፡ ሐር ፡ የተጠ
ለፈ ፡ ዕቃና ፡ ሱካር ፡ ሩዝም ፡ ከፋርስና ፡ ከዐረብ ፡ አገር ፡ ታገኝ ፡ ነበር ።
፮ ፤ አራዊትንና ፡ ከአራዊት ፡ ጋር ፡ የሚያስታግሉዋቸውን ፡ ሰዎች ፡ ለማሳየት ፡
አስቀድሞ ፡ የጨዋታ ፡ ቤት ፡ የተሠራው ፡ በሮም ፡ ነው ። ሲሠራም ፡ ለጊዜው ፡
ተብሎ ፡ በዕንጨት ፡ ብቻ ፡ ተደርጎ ፡ ተሠርቶ ፡ ነበር ። ምናልባት ፡ የተሠራው ፡
በጁሊውስ ፡ ቄሣር ፡ ዘመን ፡ ይሆናል ። በቫስጳሲያን ፡ መንግሥት ፡ ጊዜ ፡ ተጀምሮ ፡
የተሠራው ፡ ኰሊሲውም ፡ የተባለው ፡ የፍላጴያኖች ፡ የጨዋታ ፡ ቤት ፡ በጣም ፡
የታወቀ ፡ ነው ። ከስምንት ፡ ሺሕ ፡ ሰው ፡ በላይ ፡ ይይዝ ፡ ነበር ፡ ይባላል ።
፯ ፡ በዚያው ፡ መኻከል ፡ ዋሻ ፤ ወይም ፡ ጕሬ ፡ እየተደረገላቸው ፡ አራዊት ፡ የሚኖ
ሩበት ፡ ስፍራ ፡ ነበር ። አውሬዎቹ ፡ የሚመለከቱዋቸውን ፡ እንዳይጣሉ ፡ ብለው ፡ ዙሪ
ያውን ፡ አጥርና ፡ ቦይ ፡ ተደርጎ ፡ ነበር ። ለዚህ ፡ እርስ ፡ በራሳቸው ፡ እየተናከሱ ፡
ሲተላለቁ ፡ በማየት ፡ ለሚያስቅቀው ፡ ብለው ፡ ብዙ ፡ የዱር ፡ አራዊት ፡ ሰብስ
በው ፡ ነበር ።
፰ ፤ ዲሲያን ፡ የተባሉትን ፡ ሕዝብ ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ እንደ ፡ ገቡ ፡ ጊዜ ፡ ድል ፡ አድ
ራጊውን ፡ ለማክበር ፡ ተብሎ ፡ ባራት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ፲፪ ፡ ሺሕ ፡ ታረዱ ፡ ይባላል ።
እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ ይህንኑ ፡ በመሰለ ፡ በሌላው ፡ ድል ፡ ጊዜ ፡ በጥቂት ፡ ቀን ፡
ውስጥ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ አንበሶች ፡ ተገድለዋል ።
፱ ፤ አራዊትና ፡ ሰዎች ፡ በሮም ፡ አደባባይ ፡ መታገል ፡ የጀመሩት ፡ ከከተማዪቱ ፡
መመሥረት ፡ ፲፫ኛው ፡ መቶ ፡ ሲቃረብ ፡ ነው ። በመቃብር ፡ ምክንያት ፡ የተሰበሰበውን ፡
ሰው ፡ ለማሳየት ፡ ብለው ፡ አውሬና ፡ ሰው ፡ ያስታግሉ ፡ ነበር ። ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡
እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ የተለመደ ፡ ሆነና ፡ ባመት ፡ ባል ፡ ቀን ፡ ሁልጊዜ ፡
አውሬና ፡ ሰው ፡ ማስታገል ፡ የተለመደ ፡ ሆነ ።

፲ ፤ ለሕዝብ ፣ መሣቂያና ፣ መሣለቂያ ፣ ለማድረግ ፣ በአደባባይ ፣ እንዲታዩ ፣ አም ስት ፣ መቶ ፣ ጥንድ ፣ የሚሆኑ ፣ ሰውና ፣ አራዊት ፣ እርስ ፣ በርሳቸው ፣ ሲታገሉ ፣ ለማየት ፣ ወደ ፣ አደባባያቸው ፣ እየነዱ ፣ ያወጡዋቸዋል ። ከአውሬ ፣ ጋር ፣ የሚ ያታግሉዋቸውም ፣ መጀመሪያ ፣ ከጦርነት ፣ የተማረኩትን ፣ ወይም ፣ ዐመጸኞችንና ፣ ነፍሰ ፣ ገዳዮችን ፤ አለዚያም ፣ ከሠለጠኑዋቸው ፣ ባሮች ፣ ወገን ፣ የሆኑትን ፣ ነው ።

፲፩ ፤ በልዩ ፣ ልዩ ፣ መሣሪያ ፣ ያዋጉዋቸዋል ። እኩሌቶችንም ፣ ሙሉ ፣ መሣሪያ ፣ ሰጥተው ፣ ያዋጓቸዋል ። ለሌሎችም ፣ የሚጠልፉበት ፣ ገመድ ፣ የመሰለ ፣ ሰጥተው ፣ በዚያ ፣ ብቻ ፣ ተብትበው ፣ አውሬውን ፣ እንዲገድሉ ፣ ያደርጉዋቸዋል ።

፲፪ ፤ የሚሠሩት ፣ ሁሉ ፣ የአረመኔና ፣ የጭካኔ ፣ ሥራ ፣ ነበር ፣ እንጂ ፣ የሰውነት ፣ ሥራ ፣ አልነበረም ። ይህም ፣ እጅግ ፣ የእንስሳ ፣ ሁኔታ ፣ እንደ ፣ ነበራቸውና ፣ የተዋ ረዱ ፣ መሆናቸውን ፣ ያሳያል ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ የሮማውያን ፣ የመጀመሪያው ፣ መርከባቸው ፣ እንዴት ፣ ያለ ፣ ነው ፣ ?

፪ ፤ ስለ ፣ ጦር ፣ መርከቦች ፣ ተናገር ።

፫ ፤ ሮሞች ፣ የንግድ ፣ መርከባቸው ፣ እንዴት ፣ ያለ ፣ ነው ፣ ይባላል ፣ ? የመርከብ ፣ ጕዞስ ፣ ? የመርከቦች ፣ መቆሚያ ፣ እንዴት ፣ ያለ ፣ ነው ፣ ?

፬ ፤ ከምሥራቅ ፣ የሚገኘውን ፣ ጥቅም ፣ ሮም ፣ እንዴት ፣ አገኘው ፣ ?

፭ ፤ ወደ ፣ ጣሊያን ፣ አገር ፣ የሚገባው ፣ ገቢ ፣ ንግድ ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ?

፮ ፤ ቀድሞ ፣ ሰውንና ፣ አውሬን ፣ ስለሚያስታግሉበት ፣ ጨዋታ ፣ ምን ፣ ይባላል ፣ ?

፯ ፤ የዱር ፣ አራዊት ፣ እንደምን ፣ ጠፉ ፣ ?

፱ ፤ ሰውንና ፣ አውሬን ፣ ማስታገል ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ?

፲፩ ፤ ከአራዊት ፣ ጋር ፣ የሚታገሉ ፣ ሰዎች ፣ የሚይዙት ፣ መሣሪያ ፣ እን ዴት ፣ ያለ ፣ ነው ፣ ? በዚያ ፣ ስለሚታየው ፣ ሁሉ ፣ ምን ፣ ይባላል ፣ ?

## ምዕራፍ ፣ ፱፲፭ ፣ ኤውሮጳ ።

### ጨዋታ ፣ የሠረገላ ፡ እሽቅድድም ፣ የመጨዋቻ ፣ ቤት ።

### መንኰራኵሮች ፣ ልዩ ፣ መጨዋቻ ፣ የመብል ፣ ቤት ፣ ተድላ ፣ ደስታ ።

፩ ፤ ደግሞ ፣ ታሪኩን ፣ ለውጬ ፣ ስለ ፣ ሮማውያን ፣ የአራዊትነት ፣ ጨዋታ ፣ ዝቅ ፣ ያለ ፣ አሳብ ፣ እሰጣችኋለሁ ። በኛ ፣ ዘንድ ፣ በእጅም ፣ በእግርም ፣ ኳስ ፣ እንደምንጫወት ፣ እንዲሁም ፣ የኳስ ፣ ጨዋታ ፣ በብዙ ፣ ዐይነት ፣ አድርገው ፣ ይጫወታሉ ፣ ብዙ ፣ ዐይነት ፣ ጨዋታ ፣ አላቸው ። ኃይልና ፣ ብርታት ፣ ጥንክርናም ፣ እንዲያገኙ ፣

ጐበዛዝት ፡ የሚጫወቱት ፡ በሜዳ ፡ ላይ ፡ ነው ። በጡጫ ፡ መማታት ፣ መታገልና ፡ መወራወርም ፡ ሁሉ ፡ የጨዋታቸው ፡ ክፍል ፡ ነው ። ሠረገላ ፡ መንዳት ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ነው ።

፬ ፣ በፈረስና ፡ በሠረገላ ፡ መሽቀዳደምን ፡ ለማየት ፣ የከተማውን ፡ ሕዝብ ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ የተሠራ ፡ ስርኩስ ፡ የሚሉት ፡ ዙሪያውን ፡ በአጥር ፡ የተከበበ ፡ ሰፊ ፡ ሜዳ ፡ አለ ። ዙሪያው ፡ ከንድ ፡ ማይል ፡ ይበልጣል ። በዚህም ፡ ስፋት ፡ ሦስት ፡ ዙሪያ ፡ ሆኖ ፡ የሰው ፡ መቀመጫ ፡ ተሠርቶአል ።

፭ ፣ ሰውን ፡ አደጋ ፡ እንዳያገኘው ፡ ተመኻከሉ ፡ ፲፬ ፡ ፊት ፡ ርዝመት ፡ ፱ ፡ ፊት ፡ ከፍታ ፡ ያለው ፡ መከላከያ ፡ አለው ። እሽቅድድሙ ፡ የሚደረገው ፡ ከዚህ ፡ መከላ ከያ ፡ ውጪ ፡ ነው ፣ ባንድ ፡ ወገን ፡ ብቻ ፡ ቀስተ ፡ ደመና ፡ ( ቀስት ፡ ) አለው ። በዚህ ፡ ቀስተ ፡ ደመና ፡ በሽቅድድም ፡ ድል ፡ ያደረገ ፡ ሠረገላ ፡ ሲያልፍ ፡ ዙሪያውን ፡ የተቀመጠው ፡ የከተማው ፡ ሠራዊት ፡ ጭብጨባና ፡ እልልታ ፡ ያደባልቁለታል ።

፮ ፣ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀለም ፡ ያለው ፡ ልብስ ፡ የለበሱ ፡ ሠረገላ ፡ ነጂዎች ፡ መቸውንም ፡ ለመሽቀዳደም ፡ ሲያስነሡ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። እያንዳንዱ ፡ ልዩ ፡ ቀለም ፡ ያለው ፡ ልብስ ፡ የለበሰው ፡ የሚወራረድ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ አለው ። ጨዋታው ፡ ሕዝብ ፡ የለ መደው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ መጨረሻ ፡ የለውም ።

፯ ፣ ሮማውያን ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ መንኰራኵሮች ፡ እንደ ፡ ነበሩዋቸው ፡ እውነተኛ ፡ መግለጫ ፡ አላገኘንም ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ መንኰራኵሮች ፡ ነበሩ ዋቸው ። አንዳንዶቹ ፡ ተላይ ፡ ክፍት ፡ የሆኑ ፣ ሌሎቹም ፣ ባለመሸፈኛ ፡ የሆኑ ፣ አንዳንዶቹ ፡ ደግሞ ፡ በመሸከሚያ ፡ አድርገው ፡ ባሮች ፡ የሚሸከሙዋቸው ፡ ናቸው ። ሠረገላው ፡ ፍራሽና ፡ ትራስ ፡ ያለው ፡ ነው ። ሲዘረጋ ፡ የብርና ፡ የወርቅ ፡ እግር ፡ አለው ። በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ ቀለም ፡ የተሸለመ ፡ አልጋ ፡ ያላቸው ፣ በበቅሎ ፡ የሚሳቡ ፡ ሁለት ፡ ወይም ፡ አራት ፡ መንኰራኵር ፡ ያላቸው ፡ ሠረገሎች ፡ ነበሩ ።

፰ ፣ ጐባጣ ፡ ዕንጨት ፡ ባንገታቸው ፡ አግብተው ፡ ፈረሶቻቸውን ፡ ጋሪ ፡ ይጠምዱ ዋቸዋል ። የፈረሶቹ ፡ ዕቃ ፡ በሐር ፡ የተጠለፈ ፡ ሆኖ ፡ የወርቅ ፡ ልጓም ፡ ተለጕ መው ፡ ዛቡን ፡ ይዘው ፡ ይመሩዋቸዋል ። ጋሪ ፡ ለመጐተት ፡ ፈረስና ፡ በቅሎም ፡ ባይሆን ፡ ሌሎችም ፡ እንስሶች ፣ ውሾች ፣ ፍየሎች ፣ ድኵላዎች ፣ ነብሮች ፡ አን በሶችም ፡ ይሆናሉ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ስለ ፡ ተባለ ፡ ለጨዋታ ፡ ጕዳይ ፡ ሲሆን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለቁም ፡ ነገር ፡ ሥራ ፡ አይሆኑም ።

፱ ፣ ቀድሞ ፡ ሮማውያን ፡ በድህነታቸው ፡ ዘመን ፡ ሲኖሩ ፡ ምግባቸው ፡ ወተትና ፡ ቅጠላቅጠል ፣ ሻከራ ፡ ዱቄት ፡ በውሃ ፡ አድርገው ፡ ይመገቡ ፡ ነበሩ ። ነገር ፡ ግን ፡ እያደር ፡ ኃይል ፡ ካገኙና ፡ ጐረቤቶቻቸውን ፡ እየወጉ ፡ ድል ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ ካሸነፉዋቸው ፡ ሕዝብ ፡ የተድላንና ፡ የአዱኛን ፡ ነገር ፡ ተማሩ ። እነዚያ ንም ፡ ወደ ፡ መንግሥታቸው ፡ አስተዋወቁዋቸው ።

፰፡ ከግሪክ፡የረቂቅ፡ ብልሀትን፡ምሳሌ፡ስለ፡አገኙ፡እንዲሁም፡እስያዎች፡ ለአእምሮ ዋቸው፡ ደስ፡ የሚያሰኙን፡ ብዙ፡ ነገሮችን፡ አወጡ ። በኋላም፡ በሬፑብሊክ፡ ዘመን፡ ስለ፡ ምግብ፡ማስናዳት፡ነገር፡ ብዙ፡ ጥንቃቄ፡ ተደረገ ። ብዙ፡ማኅበሮች፡ ተሰብስበው፡ በሚጫወቱበት፡ ደስ፡ ለማሰኘት፡ በብዙ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ክፍል፡ ያሉ፡የሀብታሞች፡ ቤቶች፡ ምግብ፡የማዘጋጀትን፡ ብልሀት፡ ተምረው፡ ለመዱ ።

፱፡ ያንዳንዶቹ፡ ነገሥታት፡ የመብል፡ ቤት፡ በወርቅና፡ በብር፡ በፈርጥም፡ያጌጠ፡ መጋረጃ፡ ተሰቅሎበታል ። ገበታቸው፡ ፍጹም፡ ከጥሩ፡ ወርቅ፡ የተሠራ፡ ነው ። መቀመጫቸው፡ በብር፡ ያጌጠ፡ ነው ። ሮማውያን፡ መቸውንም፡ ሲመገቡ፡ ሳሉ፡ መጨጊያ፡ ተደግፈው፡ ነው ።

፲፡ ታላቅ፡ ጨዋታ፡ ወግ፡ በሚደረግበት፡ ቀን፡ የመብል፡ ቤቱን፡ በአበባ፡ ያስ ጌጣሉ ። የተጠሩት፡ ወይም፡ የሚሰበሰቡት፡ እንግዶችም፡አበባውንና፡ ቅጠሉን፡ እንደ፡ ዘውድ፡ አድርገው፡ ሠርተው፡ በራሳቸው፡ ላይ፡ እያደረጉ፡ ይመጣሉ ። ምንም፡ በብዙ፡ ጌጥ፡ ቢያስጌጡት፡ ብዙ፡ ጊዜ፡ በወለሉ፡ ላይ፡ ምንጣፍ፡ አያነጥፉበትም ። ጣራውን፡ ተወደውስጥ፡ በወርቅና፡ በዝሆን፡ ጥርስ፡ ያስጌጡ ታል ። በየክፍሉ፡ ሽታ፡ ያለው፡ ዘይት፡ ያበራሉ ። ማብሪያውም፡ በልዩ፡ ልዩ፡ መልክ፡ እየተቀረጸ፡ ደስ፡ በሚያሰኝ፡ ሁኔታ፡ እያብለጨለጨ፡ ደስ፡ የሚያሰኝ፡ ብርሃን፡ ይሰጣል ።

፲፩፡ አንዳንዶቹ፡ ለፍትወት፡ የተሰጡ፡ የተዋረዱ፡ የሮማውያን፡ ነገሥታት፡ በሬፑብሊክ፡ መበላሸት፡ ማዕዳቸው፡ እጅግ፡ የተበላሸና፡ የሚያሥቅ፡ ነው ። በየዕለቱ፡ የሚመገቡት፡ የወፎች፡ አንጐል፡ የፓሮት፡ ጭንቅላት፡ የፒኮክና፡ የናይቴንጋል፡ መላስ፡ ያለበት፡ ነው ።

፲፪፡ ዋናው፡ የተከበረውና ደስ፡ የሚያሰኘው፡ የሮማውያን፡ ማዕድ፡ ከዶሮ፡ ሥጋና፡ ከሴላም፡ ጋር፡ የተጠበሰ፡ ያማማ፡ ሥጋ፡ ነው ። ጌቶቻቸው፡ ሀብታ ቸውን፡ ለእንደዚህ፡ ያለ፡ ፍትወት፡ ሲያጠፉ፡ የሕዝቡ፡ ንብረት፡ እንዴት፡ የሚያሳዝን፡ ነበረ፡ ይመስላችኋል ።

፲፫፡ በተሻለ፡ አኳኋን፡ እየተሰናዳ፡ ልክ፡ የሌለው፡ ዓሣ፡ ወደ፡ ንጉሡ፡ እንዲ ቀርብ፡ አማከሮቹ፡ ለመመካከር፡ ይሰበሰቡ፡ ነበር ። በኛ፡ ጊዜ፡ ግን፡ የወጥ፡ ቤቶች፡ ማኅበር፡ የሚጠሩት፡ ለብርቱ፡ ጉዳይና፡ ነገሩ፡ ወደ፡ ሕዝብ፡ገገሮች፡ የሚደርስ፡ የሆነ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ነው ።

፲፬፡ ንጉሣቸውና፡ አማካሮቻቸው፡ ስለ፡ ዓሣው፡ ሥራ፡ እንዳደረጉት፡ ሠር ተው፡ ቢሆን፡ ሮማውያን፡ ባርነታቸውና፡ ውርደታቸው፡ እየቀለለላቸው፡ ይሄድ፡ ነበር ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩፡ የሮም፡ ጉበዛዝት፡ ጨዋታ፡ እንዴት፡ ነው፡ ?

፪፡ ሕዝቡ፡ ተሰብስበው፡ ጨዋታ፡ የሚታይበት፡ስፍራ፡እንዴት፡ያለ፡ነው ?

፬ ፤ ሠረገላዎችና ፣ ነጂዎች ፣ ምን ፣ መለዮ ፣ አላቸው ፣?

፭ ፤ የሮማውያን ፣ ሠረገሎች ፣ ምን ፣ ይመስላሉ ፣ ይባላል ፣?

፮ ፤ የፈረሶች ፣ ዕቃና ፣ መሣሪያ ፣ እንዴት ፣ ያለ ፣ ነው ።

፯ ፤ ከፈረስና ፣ ከበቅሎ ፣ አጋሰስ ፣ ሌላ ፣ ለጭነት ፣ የሚሆኑ ፣ እንስሶች ፣ አሉዋቸውን ፡ ?

፰ ፤ የቀድሞ ፣ የሮማውያን ፣ ኑሮ ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ? ተድላና ፣ ደስታ ፣ በምን ፡ አገኙ ፣ ?

፱ ፤ የወጥ ፣ ሥራ ፣ ብልሀታቸው ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ?

፲ ፤ የመብል ፣ ጓዳቸው ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ?

፲፩ ፣ የመብል ፣ ጓዳ ፣ ሽልማት ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ?

፲፪ ፤ የሮም ፣ ቄሣር ፣ የከበረ ፣ ማዕድ ፣ እንዴት ፣ ያለ ፣ ነው ፣ ?

፲፫ ፤ ስለ ፣ ማዕድ ፣ ጉዳይ ፣ የሚደረገውን ፣ ምክርና ፣ ጉዳይ ፣ ተናገር ።

፲፬ ፣ ሮማውያን ፣ እንዴት ፣ ሆኑ ፣ ?

## ምዕራፍ ፣ ፻፲፯ ፣ ኤውሮጳ ።

### ስለ ፣ ጨዋታ ፣ ቤትና ፣ ስለ ፣ ሰዓት ስለ ፣ ረቂቅ ፣ ሥራና ፣
### ስለ ፣ መጻሕፍት ፣ አጻጻፍ ፣ ልማድ ፣ መጨረሻ ።

፩ ፤ የቲያትር ፣ ጨዋታ ፣ መጀመሪያ ፣ በሮም ፣ የታወቀው ፣ ከተማው ፣ በተሠራ ፣ በ፫፻፷፬ ፣ ዓመት ፣ ነው ። መጀመሪያ ፣ ትንሽ ፣ ጭፈራና ፣ ቀሽንት ፣ መሳይ ፣ እየነፉ ፣ ይጫወቱ ፣ ነበር ። የቲያትር ፣ ጨዋታ ፣ ሳይለመድ ፣ ከመቶ ፣ ዓመት ፣ ይበልጥ ፣ ቈይቷል ።

፪ ፤ ሠሪዎቹ ፣ ሁልጊዜ ፣ በንቃት ፣ ሲሠሩ ፣ ወደ ፣ መቻል ፣ ደረሱ ። ከሚደግፉዋቸው ፣ ብዙ ፣ ገንዘብ ፣ አገኙ ። መጀመሪያ ፣ (ቲያትር ፣) የጨዋታ ፣ ቤት ፣ የተሠራው ፣ በመንደሮች ፣ አጠገብ ፣ ነው ። መጀመሪያ ፣ የጨዋታ ፣ ቤት ፣ በከተማው ውስጥ ፣ ቀዋሚ ፣ ሆኖ ፣ የተሠራው ፣ በድንጋይ ፣ ነው ። ሲሠሩትም ፣ ፵ ፣ ሺሕ ፣ ሰው ፣ እንዲይዝ ፣ አድርገው ፣ ነው ።

፫ ፤ ዛሬ ፣ በየኪሳችን ፣ እንደምንይዘውና ፣ በየቤታችን ፣ በገበታ ፣ ላይ ፤ ወይም ፣ በግድግዳ ፣ ላይ ፣ እንደምንሰቅለው ፣ ያለ ፣ ትልልቅ ፣ ሰዓት ፣ በሮማውያን ፣ ዘንድ ፣ ያልታወቀ ፣ ነበር ። ከተማው ፣ ሮም ፣ ከተመሠረተ ፣ በኋላ ፣ ፬፻፺፩ ፣ ዓመት ፣ በፀሓይ ፣ ሰዓት ፣ የሚቈጥሩበትን ፣ ብልሀት ፣ አገኙ ። ከመቶ ፣ ዓመት ፣ በኋላ ፣ የሰዓትን ፣ ልክ ፣ ሁሉ ፣ የሚያስታውቃቸውን ፣ ወትርክሎክ የሚሉትን ፣ አገኙ ።

፬ ፤ ስድስት ፣ መቶ ፣ ዓመት ፣ ቈይተው ፣ ካሸነፉዋቸው ፣ አገሮች ፣ እስቲማሩት ፣ ድረስ ፣ ሮማውያን ፣ ጭራሽ ፣ የብልሀት ፣ ሥራ ፣ የሚሉትን ፣ አያውቁም ፣ ነበር ። የብልሀትንም ፣ ሥራ ፣ ካወቁ ፣ በኋላ ፣ በየታላላቁ ፣ ቤታቸው ፣ ዙሪያ ፣ ምሽግ ፣ መመሸግ ፣ ጀመሩ ። ወዲያው ፣ ቀለም ፣ እየቀቡ ፤ ደንጊያም ፣ እየጠረቡ ፣ ማስጌጥ ፣ ጀመሩ ።

፭ ፤ ሀብታሞች ፡ በሚኖሩበት ፡ ስፍራ ፡ በነዚህ ፡ ምሽጎች ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ ለማኖር ፡ ምቹ ፡ ሆነ ። ዋጋቸው ፡ ስለ፡በዛ ፤ ወይም ፡ ለመገልበጥ ፡ ብዙ ፡ ኪሳራ ፡ ያለበት ፤ ስለ፡ሆነ ፡ ብዙ፡መጻሕፍትን ፡ ለመሰብሰብ ፡ ችግር ፡ ነበር ።

፮ ፤ መጻሕፍት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፤ በብራና ፡ ይጻፉ ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የሚበዙት ፡ መጻሕፍት ፡ ከእታክልት ፡ ቅጠል ፡ በሚሠሩት፡ወረቀቶች፡ይጻፉ ፡ ነበር ። ወረቀቶቹን ፡ በመጣበቅ ፡ አንድነት ፡ አጣብቀው ፡ በሐር ፤ ወይም ፡ በሲባጎ፡ ይጠርዙትና ። ውጪውን ፡ በቆዳ ፡ ይሸፍኑታል ።

፯ ፤ ዛሬ ፡ እኛ ፡ እንደምናደርገው ፡ መቃውን ፡ ሠንጥቀው ፤ ጫፉን ፡ አሹለው ፡ ቀለም ፡ እየጠቀሱ ፡ ይጽፉሉ ። ቀለም ፡ በተቀባ ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ በሾለ ፡ ነገር ፡ ይጽፉሉ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ነገር ፡ የለም ። ወረቀት ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ሲጻፍ ፡ ሽቱ ፡ ከተደረገበት ፡ በኋላ፡ በሐር ፡ ክር ፡ ይታሰርና ፡ ከጫፉ ፡ ላይ ፡ ሰም፡ አድርጎ ፡ በማኅተም ፡ ይረገጣል ።

፰ ፤ ሮማውያን ፡ ዘወትር ፡ የሚለብሱዋቸው ፡ አንዱ ፡ ቶጋ ፤ ሁለተኛው ፡ ቱኒክ ፡ የሚሉዋቸው ፡ ቀሚሶች ፡ አሉዋቸው ። ቶጋ ፡ ከጥጥ ፡ የተሠራ ፡ ሆኖ ፡ እጅጌ ፡ የሌለው ፡ ሰፊ ፡ ቀሚስ ፡ ነው ። ቱኒክ ፡ ወደ፡ሩቅ ፡ አገር ፡ በሄዱ ፡ ጊዜ ፡ በውስጥ ፡ ይለበስና ፡ በላይ ፡ ቶጋ ፡ ይደረባል ። በቤት ፡ ውስጥ ፤ ግን ፡ ቱኒክ ፡ ብቻውን ፡ ይለበሳል ። ወንዶች ፡ ሁልጊዜ ፡ ባርኔጣ ፡ አያደርጉም ።

፱ ፤ ለእግራቸው ፡ ቡስኪን ፤ ወይም ፡ ነጠላ ፡ ጫማ ፤ ያደርጋሉ ። ነጠላ ፡ ጫማ፡ ለታች፡ ብቻ ፡ የሚሆን ፡ ነውና ፤ በዘለበት፡ይቈልፉታል ። ቡስኪ ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ቅልጥም ፡ ይደርሳል ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ የቲያትር ፡ ጨዋታ ፡ በሮም ፡ የታወቀ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?

፪ ፤ ስለ ፡ ጨዋታው፡ምን፡ይባላል ፡ ? ጨዋታውንስ ፡ የሚያሳዩ ፡ ? ቲያትር ፡ ?

፫ ፤ የሰዓት ፡ ዐይነት ፡ ?

፬ ፤ ስለ፡እደ፡ጥበብ ፡ ምን ፡ ይባላል ፡ ? ስለ፡መጻሕፍት ፡ ? ወረቀት ፡ ? ጽሕፈት ፡ ? ደብዳቤ ፡ ?

፭ ፤ የሮማውያን ፡ የዘወትር ፡ ቀሚስ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፻፲፯ ፡ ኤውሮጳ ።

### ሮም ፡ ከጳጳስ ፡ በታች ፡ እንደ ፡ ሆነች ።

፩ ፤ አሁን ፡ ወደ፡ሮም ፡ ታሪክ ፡ መጨረሻ ፡ መድረሴ ፡ ነው ። ከሁን ፡ ቀድም ፡ ስለ ፡ ሮም ፡ ጳጳስ ፡ ለመናገር ፡ ምክንያት ፡ ነበረኝ ። ይህ ፡ ማዕርግ ፡ አስቀድሞ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለጳጳሳት ፡ ተሰጥቶ ፡ ነበር ። መጀሪያ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡

አለቃ ፡ የነበረው ፡ የሮም ፡ ጳጳስ ፡ ብቻ ፡ ነበር ። እያደር ፡ በቀን ፡ ብዛት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ራስ ፡ ወደመባል ፡ ደረሰ ። ወዲያው ፡ ከቄሣሮችና ፡ ከነገሥታት ፡ ጋራ ፡ በላይነትን ፡ ለማግኘት ፡ ተፋለመ ።

፪ ፡ የሮም ፡ ጳጳስ ፡ ረጅም ፡ ዘመን ፡ ለሃይማኖት ፡ ጉዳይ ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፡ ሥልጣን ፡ ነበረው ። ነገር ፡ ግን ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ሦስተኛ ፡ የኢጣሊያንን ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ይገዛ ፡ የነበረውን ፡ የግሪክን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሽረና ፡ የጳጳስ ፡ ሥልጣን ፡ የመንግሥቱን ፡ ጉዳይ ፡ እንዲያከናውን ፡ አደረገ ። ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ወደፊት ፡ ጳጳሳት ፡ በፍጥነት ፡ ኃይል ፡ አገኙ ፡ በ፭፻፹፪ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ብዙ ፡ ገንዘብና ፡ ሀብት ፡ ሰበሰቡ ። ትዕቢታቸው ፡ ከገንዘባቸው ፡ ጋራ ፡ ትክክል ፡ ሆነና ፡ ወሰን ፡ ጠፋበት ።

፫ ፡ ጳጳሳት ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የእግዚአብሔር ፡ እንደራሴ ፡ (ምስለኔ) ፡ መባልን ፡ ስለ ፈለጉ ፡ ራሳቸውን ፡ የቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ (እንደራሴ) ፡ ወራሾች ፡ አድርገው ፡ የመ ንግሥተ ፡ ሰማይና ፡ የሲኦል ፡ መክፈቻ ፡ ተሰጥቶናል ፡ ይላሉ ። በሰዎች ፡ ነፍሳት ፡ ላይ ፡ በግፍ ፡ ገዝተዋልና ፡ እንደነሱ ፡ ግፈኛ ፡ ገዢ ፡ አልነበረም ።

፬ ፡ ሌሎች ፡ ነገሥታት ፡ ዘውድ ፡ ቢጭኑ ፡ አንድ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ጳጳሳት ፡ ግን ፡ አንዱን ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ እያደራረቡ ፡ ሦስቱን ፡ ዘውድ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይጭናሉ ። ለራሳቸው ፡ የቅዱሳንን ፡ ማዕርግና ፡ ስም ፡ ስለ ፡ ወሰዱ ፡ ይህንንም ፡ ዘውድ ፡ ቲያራ ፡ ይሉታል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ከነሱ ፡ አያሎቹ ፡ ቅድስና ፡ የሌላቸው ፡ በምድራዊ ፡ ነገር ፡ የተያዙ ፡ ኃጢአት ፡ የነበዛቸው ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ።

፭ ፡ ሥልጣናቸው ፡ ያለመጠን ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ የትዕቢትና ፡ የመነፋት ፡ መልክ ፡ ያሳያሉ ። በፊታቸው ፡ ቀርቦ ፡ ተንበርክኮ ፡ ጫማቸውን ፡ ለመሳም ፡ ለማንም ፡ ሰው ፡ አይፈቀድለትም ። በፈረስ ፡ ሲቀመጡ ፡ ነገሥታቱን ፡ እርካብ ፡ ያሲዙዋቸዋል ።

፮ ፡ ለዙፋኑ ፡ የተገቡትን ፡ ነገሥታት ፡ እየሻሩ ፡ መንግሥታቸውን ፡ ለሌሎች ፡ ላል ተገባቸው ፡ ሰዎች ፡ ይሰጡባቸው ፡ ነበሩ ። ክሌሜንት ፡ የተባለው ፡ ጳጳስ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ የሰማይንና ፡ የምድርን ፡ መንግሥታት ፡ ሁሉ ፡ ሰጠኝ ፡ ብሎ ፡ አሳውጆ ፡ ነበር ። ማንም ፡ የጳጳስን ፡ ሥልጣን ፡ የሚቃወም ፡ ሰው ፡ ቢገኝ ፡ በሕይወቱ ወደ ፡ እሳት ፡ ተጥሎ ፡ ይቃጠል ፡ ነበር ።

፯ ፡ በ፲፻፷፱ ፡ ዓመት ፡ ጳጳሱ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ አራተኛ ፡ ሄንሪ ፡ የተባለውን ፡ የጀርመንን ፡ ንጉሥ ፡ ይቅርታ ፡ እንዲያደርግለት ፡ ባደባባዩ ፡ በክረምት ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ እውጪ ፡ እቅዝቃዜ ፡ ላይ ፡ አሳድሮታል ።

፰ ፡ ከሮም ፡ ጳጳሶች ፡ አንዱ ፡ የሮም ፡ ጳጳስ ፡ ሥልጣን ፡ የሚሰጠው ፡ ለሮም ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሥርዓት ፡ ያደረገውና ፡ የጳጳሳት ፡ ሥልጣን ፡ እጅግ ፡ ያለመጠን ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የነበረው ፡ ቅርብ ፡ በ፲፩፻ ፡ ዓመት ፡ ነበር ። ሌላው ፡ ይቅርና ፡ በክርስቲያን ፡ ዓለም ፡ ያሉ ፡ ነገሥታትና ፡ መኳንንት ፡ በጳጳስ ፡ አገዛዝ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ክርክር ፡ ሳያደርጉበት ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ የሚሆን ፡ ረግጦ ፡ ገዝቶአቸዋል ።

፱ ፤ በዚሁ ፡ ዘመን ፡ በሙሉ ፡ ኤውሮጳ ፡ በእስያና ፡ በአፍሪካ ፤ ታላቅ ፡ ጨለማ ፡ ወድቆባቸው ፡ ነበር ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ሮም ፡ የጳጳስ ፡ መኖሪያ ፡ ብትሆን ፡ ሕዝቡ ፡ በድንቍርናና ፡ በውርደት ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ።

፲ ፤ ግን ፡ በ፲፭፻፲፯ ፡ ዓመት ፡ ማርቲን ፡ ሉተር ፡ በሚባል ፡ ሰው ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መታደስ ፡ ተጀመረ ። ይህም ፡ የሮም ፡ ጳጳሳትን ፡ ሥልጣን ፡ በመቃወም ፡ ይሰብክ ፡ ጀመር ። ስለዚህ ፡ መላው ፡ ኤውሮጳ ፡ ተናወጠና ፡ በክርስቲያን ፡ ዓለም ፡ ያሉት ፡ መንግሥታት ፡ የጳጳሳትን ፡ ሥልጣን ፡ አምዘግዝገው ፡ ጣሉት ። በዚሁ ፡ ሁከት ፡ የተነሣ ፡ ጦርነት ፡ ተደርጎ ፡ አምስት ፡ ሚሊዮን ፡ ሰው ፡ ተገድሏል ።

፲፩ ፤ ይህ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የሮም ፡ ጳጳስ ፡ ኃይል ፡ አግኝቶ ፡ እንደ ፡ ፈቃዱ ፡ መሾምና ፡ መሻር ፤ መንግሥታትንም ፡ የማከፋፈል ፡ ችሎት ፡ ነበረው ። አሁን ፡ ግን ፡ የራሱ ፡ ነጻነት ፡ ተመልሶለታል ፡ እንጂ ፡ ግዛት ፡ የለውም ። እስከ አሁን ፡ የሮም ፡ ካቶሊክ ፡ ሃይማኖት ፡ ዋና ፡ ነው ። በኋለኛ ፡ ዘመን ፡ በ፲፰፻፷፫ ዓ. ም. የኢጣሊያ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ ገባ ። ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ሮም ፡ የኢጣሊያ ፡ ግዛት ፡ ክፍል ፡ ሆና ፡ ቀረች ።

፲፪ ፤ ዛሬ ፡ የሮም ፡ ከተማ ፡ ዙሪያ ፡ ዐሥራ ፡ ሦስት ፡ ማይል ፡ ነው ። ከዚሁም ፡ የሚበልጠው ፡ ክፍል ፡ ሰው ፡ የሌለበት ፡ ውድማ ፤ ጠፍና ፡ ደስ ፡ የማያሰኝ ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ። የቀድሞው ፡ ቤተ ፡ መንግሥቶችና ፡ ቤተ ፡ ጣዖቶች ፡ የጥንት ፡ የሮማ ፡ ሀብታሞች ፡ የሠሩት ፡ የታላላቅ ፡ ቤቶች ፡ ፍራሽ ሞልቶበታል ። ስፍር ፡ ቍጥር ፡ የሌለው ፡ ሐውልትና ፡ ከደንጊያ ፡ የተጠረበ ፡ ሥዕል ፡ ወይም ፡ ምስል ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ ሳይቀበርበት ፡ አይቀርም ።

፲፫ ፡ ይህን ፡ ምልክት ፡ እያዩ ፡ መንገደኞች ፡ በጥንት ፡ ሮማውያን ፡ ታላቅነት ፡ ይገረማሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ በጥንት ፡ ሮማውያን ፡ ጊዜ ፡ በነበሩት ፡ ኃያላንና ፡ አርበኞች ፡ ፈንታ ፡ ዛሬ ፡ መንገደኞች ፡ የሚያገኙዋቸው ፡ እጅግ ፡ ዝቅተኞችና ፡ የተዋረዱ ፡ ሕዝብ ፡ ናቸው ።

፲፬ ፤ መንፈሳቸው ፡ በብዙ ፡ ዘመን ፡ ባርነትና ፡ አምልኮ ፡ ባዕድ ፡ ደንዝዞአል ። አሁንም ፡ ቢሆን ፡ የብዙ ፡ ዘመን ፡ ግፍ ፡ እየተሰማቸው ፡ ዐመፀኝነት ፡ ተመኻከላቸው ፡ አይጠፋም ።

፲፭ ፤ ከጥንት ፡ ሮማውያን ፡ የተገኙት ፡ ቅሬታዎች ፡ እነዚህ ፡ የቤት ፡ ፍራሾች ፡ ብቻ ፡ አይደሉም ። ነገር ፡ ግን ፡ ከግሪክ ፡ ጸሓፊዎች ፡ የተገለበጡ ፤ በጥንት ፡ ሮማውያን ፡ ደራሲዎች ፡ የተጻፉት ፡ እጅግ ፡ መልካም ፡ የሆኑ ፡ ሥራዎች ፡ እስካሁን ፡ ይኖራሉ ። ቀድሞ ፡ ሮማውያን ፡ ቋንቋቸው ፡ ላቲን ፡ ነበረ ፡ ብየ ፡ እንዳስታወቅኋችሁ ፡ ይህ የተጻፈው ፡ በላቲን ፡ ነበር ። ከነዚህም ፡ ከተጻፉት ፡ አያሎች ፡ ደስ ፡ የሚያሰኙ ፡ ነገሮች ፡ አሉባቸው ። አሁን ፡ እንኳ ፡ በዘመናችን ፡ መልካም ፡ ሕግና ፡ ደንብ ፡ የሚያወጡት ፡ ከዚህ ፡ እየተመለከቱ ፡ ነው ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ ቀድሞ ፣ ዘመን ፣ ጳጳሳት ፣ እንደምን ፣ ኑረዋል ፣ ? ሦስተኛ ፣ ጎርጎርዮስ ፣ የተባለው ፣ እንዴት ፣ ያለ ፣ ሰው ፣ ነበር ፣ ? ሮም ፣ ከተመሠረተ ፣ ለጳጳሳት ፣ ሥልጣን ፣ የተሰጠ ፣ ምን ፣ ጊዜ ፣ ነው ፣ ?

በ፯፻፰ ፣ ጳጳሳት ፣ እንደምን ፣ ነበሩ ፣ ? ትዕቢታቸውና ፣ ሥልጣናቸውስ ፣ ?

፪ ፤ ጳጳሳት ፣ የሹመታቸውን ፣ ማዕርግ ፣ ምንድን ፣ ይላሉ ፣ ? ራሳቸውን ፣ ማን ፣ ያደርጋሉ ፤ ?

የግፍ ፣ አገዛዛቸው ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ?

፫ ፤ የጳጳሳት ፣ ዘውድ ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ? በምን ፤ ማዕርግ ፣ ይሰይሙታል ፣ ?

፬ ፤ ስሕተታቸው ፣ እንደምን ፣ ተገለጠ ፣ ?

፭ ፤ ጳጳስ ፣ ክሌሜንት ፣ እንዴት ፣ ያለ ፣ ሰው ፣ ነበር ፣ ? ጳጳስን ፣ በሚቃወሙ ፣ ሰዎች ፣ ላይ ፣ ምን ፣ ተደረገባቸው ፣ ?

፮ ፤ ጳጳስ ፣ ጎርጎርስ ፣ በ፲፻፸፯ ፣ ዓ. ም. ምን ፣ አደረገ ፣ ? ፲፩፻፺፩ ፣ ሌላው ፣ ጳጳስ ፣ ምን ፣ አደረገ ፣ ?

፯ ፤ በ፲፩፻ የጳጳስ ፣ ሥልጣን ፣ እንዴት ፣ ነበር ፣ ? የጳጳስ ፣ ሥልጣን ፣ ከፍ ፣ ያለ በት ፣ ምን ፣ ጊዜ ፣ ነው ፣ ?

፰ ፤ እንደዚህ ፣ ሆኖ ፣ ምን ፣ ያህል ፣ ጊዜ ፣ ኖረ ፣ ? በዚህ ፣ ጊዜ ፣ የዓለም ፣ ሁኔታ ፣ እንዴት ፣ ነበር ፣ ? ሮም ፣ እንዴት ፣ ሆነ ፣ ?

፱ ፤ በ፲፭፻፲፯ ፣ ምን ፣ ሆነ ፣ ? ማርቲን ፣ ሉተር ፣ ምን ፣ አደረገ ፣ ? በቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ መታደስ ፣ ምን ፣ ተገኘበት ፣ ?

፲ ፤ በአሁን ፣ ጊዜ ፣ የጳጳስ ፣ ሁኔታ ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ? አለቃነቱ ፣ በየ ትኛው ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ ላይ ፣ ነው ።

፲፩ ፣ አሁን ፣ ሮም ፣ ግንኙነቱ ፣ ከየትኛው ፣ መንግሥት ፣ ጋር ፣ ነው ፣ ? የዛ ሬው ፣ የሮም ፣ ከተማ ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ?

መንገደኞች ፣ ወደ ፣ ሮም ፣ በደረሱ ፣ ጊዜ ፣ እንደምን ፣ ይገረሙ ፣ ? ሕዝቡ ፣ እንደምን ፣ ያሉ ፣ ናቸው ፣ ?

፲፪ ፤ መንፈሳቸው ፣ እንዴት ፣ የሞተ ፣ ሆኗል ፣ ? የቀድሞ ፣ ሮማውያን ፣ ሥራ ፣ ምንድነው ፣ ?

በምን ፣ ቋንቋ ፣ ይጽፉ ፣ ኑረዋል ፣ ? ያሁኖቹ ፣ ከነዚህ ፣ ሥራዎች ፣ እንደ ምን ፣ ወጡ ፣ ?

## ምዕራፍ ፣ ፪፲፰ ፣ ኤውሮጳ ።

### ስለ ፣ ጥንታዊ ፣ የኢጣሊያ ፣ መንግሥት ።

፩ ፤ የኢጣሊያ ፣ ግዛትና ፣ አውራጃዎች ፣ በብዙ ፣ የተከፋፈሉ ፣ እንደ ፣ ነበሩ ፣ ታው ቃላችሁ ። እነዚሁም ፣ አውራጃዎች ፣ የየራሳቸው ፣ ታሪክ ፣ አላቸው ። የነዚህን ፣ አገ ሮች ፣ ታሪክ ፣ ወደፊት ፣ አንድ ፣ ቀን ፣ ብታነቡት ፤ አይከፋም ። በዚች ፣ ትንሽ ፣

መጽሐፍ ፡ የሁለቱን ፤ ወይም ፡ የሦስቱን ፡ አገሮች ፡ ታሪክ ፡ ባጭሩ ፡ አድርጌ ፡ አመ
ለክታችኋለሁ ። እነዚህም ፡ የሚከተሉ ፡ አውራጃዎች ፡ የናፕል ፡ ግዛትና ፡ የሲሲ
ሊን ፡ ደሴት ፡ ደግሞ ፡ የሁለቱ ፡ ሲሲሊ ፡ ግዛትና ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ተናገርሁት ፡ ጫማ ፡
የሚመስለውን ፡ አገር ፡ የኢጣሊያን ፡ ደቡብ ፡ ግዛት ፡ ጨምሮ ፡ ነው ።

፪ ፤ የናፕል ፡ ግዛት ፡ ከሮም ፡ መንግሥት ፡ ከተለየ ፡ በኋላ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ጠቀ
ሜታ ፡ አላገኘም ። በ፲፰፻፵፱ ፡ ቪክቶር ፡ ኤማኑኤል ፡ ሁለተኛ ፡ የሠርዴኛ ፡ ንጉሥ ፡
የጳጳሱን ፡ ግዛት እኩሌታ ፡ ሉምባርዲን ፡ የፓራማ ፡ ዱኪዎችንና ፡ ሞዴናን ፡
በ፲፰፻፰ ዓመት ፡ የቱስካኒን ፡ ታላቅ ፡ ዱክ ፡ ማርኬስን ፤ ኡምብሪያንና ፡ ናፕልን ፡
ሁለቱን ፡ ሲሲሊዎችንም ፡ ጨምሮ ፡ አገኘ ። በዚህ ፡ ላይ ፡ የፒዬድሞንት ፡ መንግ
ሥቱን ፡ ጨምሮ ፡ የኢጣሊያ ፡ ንጉሥ ፡ ተብሎ ፡ ነገሠ ። በ፲፰፻፸፰ ፡ ዓመት ፡ ሞተና ፡
ልጁ ፡ አንደኛ ፡ ኡምቤርቶ ፡ የተባለው ፡ ዙፋኑን ፡ ወረሰ ።

፫ ፤ የቬኒስ ፡ ታሪክ ፡ እጅግ ፡ ልብ ፡ የሚነካ ፡ ነው ። በ፬፻፶፪ ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡
አራዊት ፡ ሕዝብ ፡ ጣሊያንን ፡ በወረሩ ፡ ጊዜ ፡ አሁን ፡ ባለው ፡ በቬኒስ ፡ ከተማ ፡
ዙሪያ ፡ ይኖሩ ፡ የነበሩት ፡ ሕዝብ ፡ በረግረጉ ፡ ስፍራ ፡ በባሕር ፡ ጠረፍ ፡ ይኖሩ ፡
ነበርና ፡ ዓሣውን ፡ በጨው ፡ እያበጁ ፡ በንግድ ፡ ራሳቸውን ፡ ይረዱ ፡ ነበሩ ።

፬ ፤ በ፰፻፱ ፡ ዓ. ም. ሪያልቶ ፡ በምትባል ፡ ባንድ ፡ ትንሽ ፡ ደሴት ፡ ላይ ፡ የቬኒስን ፡ ከተማ ፡
መቈርቈር ፡ ጀመሩ ። ያላቸውን ፡ ሀብትና ፣ ጥሪት ፡ ወደዚያችው ፡ ደሴት ፡ ማጋዝ ፡
ጀመሩ ። ይህችም ፡ ከተማና ፡ አውራጃ ፡ እያደር ፡ እየተስፋፋችና ፡ እየገነነች ፡ መሄድ ፡
ጀመረች ። በዓለም ፡ ኀያላን ፡ መንግሥታት ፡ ተብለው ፡ ተሚጠሩት ፡ እንዳንዱ ፡
ሆነች ።

፭ ፤ ባላገሮቹ ፡ በንግድ ፡ እጅግ ፡ ብርቱዎች ፡ ናቸው ። አያሎች ፡ መርከቦች ፡ ነበሩዋ
ቸው ፡ ባሥራ ፡ አንደኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ የመጀሪያውን ፡ የመስቀል ፡ ጦርነት ፡
ለመርዳት ፡ ቬኒስ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ መርከቦች ፡ ሰደደች ። ይኸውም ፡ መንግሥት ፡
በባሕር ፡ ጕዳይ ፡ ደስታ ፡ ስለ ፡ ነበረው ፡ ዶግ ፡ የተባለው ፡ ጠቅላይ ፡ ሹም ፡ ሠርግ ፡
ባደረገ ፡ ጊዜ ፡ ኵራቱንና ፡ ትዕቢቱን ፡ ለማሳየት ፡ የጋብቻን ፡ ሥርዓት ፡ በባሕር ፡
ላይ ፡ ያደርገው ፡ ነበር ።

፮ ፤ የቬኒስ ፡ መንግሥት ፡ ኀይል ፡ እየበረታ ፡ ስለ ፡ ሄደ ፡ በመስቀል ፡ ጦር ፡ ርዳታ ፡ እጅግ ፡
ኀይለኛ ፡ የነበረውን ፡ የቍስጥንጥንያን ፡ ከተማ ፡ ማረከው ፥ ከተማረከው ፡
ከተማ ፡ የተገኘው ፡ ፈርጥና ፡ የከበረ ፡ ደንጊያ ፤ መጻሕፍት ፤ ዕብነ ፡ በረድ ፤ ሥዕል ፤
የተጠረበ ፡ የደንጊያ ፡ ምስል ፤ ሐውልት ፡ ሌላም ፡ ዋጋው ፡ የከበረ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡
ነበር ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ቬኒስ ፡ ተጠርጎ ፡ ሄደ ።

፯ ፤ ይህ ፡ የሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ በሀብትም ፤ በኃልበትም ፡ እንደ ፡ በረታ ፡ አያል ፡ ዘመ
ናት ፡ ቈይቶ ፡ ኖረ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ሕዝቡ ፡ በግፍ ፡ ተጨቍነው ፡ ይኖሩ ፡ ነበሩ ።
ባ፲፰ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ለፈረንሳይ ፡ ተንበረከከ ። ባ፲፯፻፺፰ ፡ ለአስትሪያ ፡ ተለቀ

ቀና ፡ አስትሪያም ፡ እስከ ፡ ፲፰፻፷፮ ሲጠብቀው ፡ ቈየ ። በአስትሪያና ፡ በፕሩሲያ ፡ መኻከል ፡ ትንሽ ፡ ግጭት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ ኢጣሊያም ፡ ተፕሩሲያ ፡ ጋር ፡ የግጭቱ ፡ ተካፋይ ፡ ስትሆን ፡ ቬኒስ ፡ ተኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ ተባበረና ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ አምሳል ፡ ሆነ ።

፰ ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የቬኒስ ፡ ተወዳዳሪ ፡ የነበረችውን ፡ የጄኔዋን ፤ የኢጣሊያ ፡ መልካም ፡ ክፍል ፡ የተባለውን ፡ የቱስካኒን ፤ የሰሜን ፡ ኢጣሊያንን ፡ ክፍል ፡ ጨምሮ ፡ የሰርዲያንን ፡ መንግሥት ፤ የናፕልን ፡ የነዚህን ፡ ሁሉ ፡ ታሪክ ፡ ብተርክ ፡ አንድ ፡ ትንሽ ፡ መጽሐፍ ፡ በሆነ ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በትንሽ ፡ መጽሐፍ ፡ ብዙ ፡ ታሪክ ፡ ለመጻፍ ፡ የማይቻል ፡ ስለሆነ ፡ ታሪኩን ፡ አሳጥሬ ፡ አልፌዋለሁ ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ አሁን ፡ ጣሊያን ፡ የተከፋፈለው ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
፪ ፤ የናፕል ፡ መንግሥት ፡ ምን ፡ ጨመረ ፡ ? የሕዝቡ ፡ ብዛት ፡ ስንት ፡ ይሆኑ ፡ ? ከሮም ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ያለው ፡ ?
፫ ፤ የኢጣሊያ ፡ የዛሬው ፡ ንጉሥ ፡ ማነው ፡ ? ላዲሱ ፡ መንግሥት ፡ የትኛው ፡ አውራጃ ፡ ተጨመረለት ፡ ?
፬ ፤ የቬኒስ ፡ ታሪክ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
፭ ፤ ቬኒስ ፡ የተሠራው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ? የተሠራውስ ፡ የት ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ? ምን ፡ ሆነ ፡ ?
፮ ፤ ንግዱ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? መርከቦቹዋስ ፡ ?
፯ ፤ የቬኒስ ፡ ኃይል ፡ ? በቬኒስና ፡ በመስቀል ፡ ጦር ፡ የትኛው ፡ ከተማ ፡ ተያዘ ፡ ?
፰ ፤ የቬኒስ ፡ ሬፑብሊክ ፡ በብዙ ፡ ዓመት ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ፈረንሳይ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ከ፲፯፻፺፰ ፡ ወዲህ ፡ ቬኒስ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፱ ፤ ጄኔቫ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ቱስካኒስ ፡ ? ሳርዲኒያስ ፡ ? እያንዳንዱ ፡ ከሮም ፡ ወዴት ፡ ናቸው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፲፱ ፡ ኤውሮጳ ።

ስለ ፡ኦቶማን ፡ መንግሥት ፡ ቱርክ ፤ በኤሮጳና ፡ በእስየ ።

ስለ ፡ አየሩና ፡ ስለ ፡ ሕዝቡ ፡ ስለ ፡ ሌላም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ።

፩ ፤ የቱርክ ፤ ወይም ፡ የኦቶማን ፡ መንግሥት ፡ በሁለት ፡ የተከፈለ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ የኤውሮጳ ፡ ቱርክ ፤ የእስያ ፡ ቱርክ ፡ እየተባለ ፡ ይጠራል ። ከዛሬ ፡ ይልቅ ፡ ቀድሞ ፡ እጅግ ፡ ሰፊ ፡ መንግሥት ፡ ነበር ። ከኤውሮጳ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ አገሮች ፡ ይዞአል ። በደቡብ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ግሪክ ፤ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ቡልጋርና ፡ ወደ ፡ ሴርቢያ ፡ ተንሰራፍቶአል ። ይኸውም ፡ ክፍል ፡ የኤውሮጳ ፡ ቱርክ ፡ ይባላል ።

፪ ፤ ትንሽ ፡ እስያንና ፡ አርመንን ፤ ሶርያንና ፡ ጳለስቲናን ፡ ጨምሮ ፡ የእስያ ፡ ቱርክ ፡ ይባላል ። ከአፍሪካ ፡ ውስጥም ፡ ግብፅና ፡ ሦስቱ ፡ የአራዊት ፡ ሕዝብ ፡ አገሮች ፡ የተባሉት ፡ ጥቂት ፡ ዘመናት ፡ ለቱርክ ፡ ተገዝተዋል ።

፫ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የኤውሮጳ ፡ ቱርክ ፤ ትንሽ ፡ እስያ ፤ አርማንያ ፤ ሶርያ ፤ ጳለስቲና ከተባሉት ፡ አገሮች ፡ በቀር ፡ ከነዚህ ፡ አገሮች ፡ ጥቂቶቹና ፡ ሌሎቹም ፡ ፈጽመው ፡ ከቱርክ ፡ ግዛት ፡ ነጻ ፡ ወጥተዋል ። ፊት ፡ እንደ ፡ ተናገርሁት ፡ አሁን ፡ እንኳ ፡ በዛሬው ፡ ዘመን ፡ ቢሆን ፡ በዓለም ፡ ካሉት ፡ ከተሞች ፡ አንዱ ፡ ታላቅ ፡ የተባለው ፡ ዋናው ፡ የኦቶማን ፡ ከተማ ፡ ቍስጥንጥንያ ፡ ነው ።

፬ ፤ የቱርክ ፡ ዋናው ፡ ገዢ ፤ ወይም ፡ ንጉሡ ፡ ሡልጣን ፡ ይባላል ። መኖሪያው ፡ በቍስጥንጥንያ ፡ በዋናው ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ነው ። እያሎች ፡ ምሥራቃውያን ፡ ነገሥታት ፡ እንደሚያደርጉት ፡ ሁለት ፡ መቶ ፤ ወይም ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሚስቶች ፡ ያኖራል ። እነዚህንም ፡ (ሀሬም ፡ )ማለት ፡ በተለየ ፡ በሴቶች ፡ ጓዳ ፡ ተዘግቶባቸው ፡ ይኖራሉ ።

፭ ፤ በእስያ ፡ ያሉት ፡ ቱርኮች ፡ ጽሕማቸውን ፡ ያስረዝማሉ ፤ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ ጥምጥም ፡ ይጠመጥማሉ ። በስተውስጥ ፡ ቀሚስ ፡ ይለብሳሉ ። ወደ ፡ ኤውሮጳ ፡ ወገን ፡ ያሉ ፡ ቱርኮች ፡ ልብሳቸውን ፡ እንደ ፡ ኤውሮጶች ፡ አድርገው ፡ ይለብሳሉ ፤ ፌዛ ፡ የሚሉትን ፡ ቀይ ፡ ቆብ ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ ይለጥፋሉ ።

፮ ፤ በገሩ ፡ ላይ ፡ ሡልጣኑ ፡ እንደ ፡ ፈቃዱ ፡ ይገዛል ፡ እንጂ ፡ የቆመውን ፡ ሕግና ፡ ደንብ ፡ አይጠብቅም ። ሕዝቡም ፡ መቸውንም ፡ ቢሆን ፡ ፈቃዱን ፡ ይፈጽሙለታል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የማይታዘዙት ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ እርግጥ ፡ ገንዘባቸውንና ፡ አንገታቸውን ፡ እንደሚያጡ ፡ ተረድተውታል ።

፯ ፤ ድንገት ፡ ወደ ፡ ቱርክ ፡ አገር ፡ ብትደርሱ ፡ አየሩ ፡ ሙቀት ፤ አገሩ ፡ ለም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ትረዱታላችሁ ። ደግሞ ፡ ባላገሮቹ ፡ ሐኬተኞችና ፡ አራዊት ፡ ሕዝብ ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፤ በገሩ ፡ ውስጥ ፡ ትንሽ ፡ ንግድ ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ ፋብሪካ ፡ እንደ ፡ ሌለበት ፡ ታገኙታላችሁ ። አገሩ ፡ በጣም ፡ አልታረሰም ፤ መሬቱ ፡ ከተፈጥሮው ፡ ፍሬ ፡ የሚሰጥ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ምድረ ፡ በዳና ፡ እዳሪ ፤ ጠፍ ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ።

፳ ፡ ሕዝቡ ፡ ክርስትናን ፡ ጠልተው ፡ የሙሐመድን ፡ ሃይማኖት ፡ እንደተቀበሉ ፡ ትረዱታላችሁ ። በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ፈንታ ፡ መስጊድ ፡ አቁመዋል ። በቍስጥ ንጥንያ ፡ ቅድስት ፡ ሶፍያ ፡ የተባለች ፡ እጅግ ፡ ያማረች ፡ ሕንፃ ፡ አለች ፡ ይህ ፡ ቀድሞ ፡ ዘመን ፡ የግሪክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ነበር ። አሁን ፡ የሙሐመድ ፡ መስ ጊድ ፡ አድርገውታል ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፡ የቱርክ ፡ መንግሥት ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ስም ፡ አለው ፡ ? የኦቶማን ፡ መንግሥት ፡ እንዴት ፡ ተከፈለ ፡ ?
የኤውሮጳ ፡ ቱርክ ፡ የሚባለው ፡ የቱ ፡ ነው ፡ ? ከትንሽ ፡ እስያ ፡ እንደምን ፡ ይዋሰናል ? ቍስጥንጥንያ ፡ ከአቴን ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ? ከኢየሩሳሌምስ ፡ ? ከሎንዶንስ ፡ ?

፪ ፡ የቱርክ ፡ መንግሥት ፡ ከሁሉ ፡ ይልቅ ፡ እጅግ ፡ የተስፋፋው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ? ቱርክ ፡ አሁን ፡ ከእስያ ፡ የጨመረው ፡ ምንድነው ፡ ?
ቀድሞ ፡ ቱርክ ፡ ይዞአቸው ፡ የነበሩ ፡ አገሮች ፡ እነየቱ ፡ ናቸው ፡ ? ትንሽ ፡ እስያ ፡ ከኤውሮጳ ፡ ቱርክ ፡ እንደምን ፡ ተለየ ፡ ?

፫ ፡ ቀድሞ ፡ የኦቶማን ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ የነበሩት ፡ አገሮች ፡ የትኞች ፡ ናቸው ፡ ? የቱርክ ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ማነው ፡ ?
ቍስጥንጥንያ ፡ ምንድነው ፡ ?

፬ ፡ ሡልጣን ፡ ምንድነው ፡ ?

፭ ፡ ስለ ፡ ቱርኮች ፡ ተናገር ፡ ?

፮ ፡ ሡልጣን ፡ ቱርክን ፡ የሚገዛው ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ ነው ፡ ? ሕዝቡ ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ?

፯ ፡ የቱርክ ፡ አገር ፡ መሬትና ፡ አየሩ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? ሕዝቡስ ፡ ? እደ ፡ ጥበባቸውስ ፡ ? ንግዱስ ፡ ? መሬቱስ ፡ ? የቱርኮች ፡ ሃይማኖታቸውስ ፡ ? መስጊዳቸውን ፡ ምን ፡ ይሉታል ፡ ? ሶፍያ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፪፳ ፡ ኤውሮጳ ።

ስለ ፡ ዐረቦች ፡ (ሳራሴን) ፡ ቱርክ ፡ የዐረቦችን ፡ መንግሥት ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ገለበጠና ፡
የኦቶማን ፡ ቱርክ ፡ የኦቶማንን ፡ መንግሥት ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ መሠረተ ፡
ስለ ፡ ባጃዜት ፡ ቲሙር ፡ ስለ ፡ ሌሎችም ፡ ሁሉ ።

፩ ፡ በእስያ ፡ ታሪክ ፡ ሳራሴን ፡ ስለ ፡ ተባሉት ፡ ዐረቦች ፡ ጥቂት ፡ አሳብ ፡ ሰጥቻችኋለሁ ፡ እነዚህም ፡ ሳራሴን ፡ የተባሉ ፡ ዐረቦች ፡ እንደሆኑ ፡ ሳታውቁ ፡ አትቀሩም ። ከነዚሁ ፡ ሙኻከል ፡ ሙሐመድና ፡ የሱ ፡ ወራሾች ፡ የሆኑ ፡ ሁሉ ፡ በሰባተኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ መጀመሪያ ፡ መንግሥት ፡ አቆሙ ።

፪ ፤ የሳራሴን ፡ መንግሥት ፡ ነገሥታት ፤ ወይም ፡ ገዦች ፡ ከሊፎች ፡ ይባላሉ ።
መኖሪያቸውን ፡ በሜሶጶታሚያ ፡ በኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ እነርሱው ፡ በሠ
ሩዋት ፡ እጅግ ፡ ባማረችው ፡ ከተማ ፡ በባግዳድ ፡ አደረጉ ። እነዚህ ፡ ከሊፎች ፡ መን
ግሥታቸውን ፡ በእስያና ፡ በኤውሮጳ ፡ በአፍሪካም ፡ ክፍል ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ዘረጉ ፡
ነግሬያችኋለሁ ።

፫ ፤ በሜሶጶታሚያ ፡ ሰሜን ፡ አያሎች ፡ የታርታር ፡ ነገዶች ፡ ነበሩ ። ከነዚሁ ፡
መኻከል ፡ አያሎቹ ፡ ቱርኮች ፡ የሚባሉ ፡ ነበሩ ። እነዚህም ፡ ድፍረታቸውና ፡
ጀግንነታቸው ፡ የታወቀላቸው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ወደባግዳድ ፡ መጥተው ፡ የወታደ
ርነት ፡ ሥራ ፡ እንዲሠሩ ፡ ከሊፎች ፡ ያባብሉዋቸው ፡ ነበሩ ።

፬ ፤ እንዲሁም ፡ በጊዜ ፡ ብዛት ፡ ቱርኮች ፡ በባግዳድ ፡ ኃይላቸው ፡ እየበረታ ፡
ስለ ፡ ሄደ ፡ በመጨረሻው ፡ የሳራሴንን ፡ መንግሥት ፡ ገልብጠው ፡ ሳራሴኖች ፡
በያዙት ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ እነርሱ ፡ ጌቶች ፡ መሆናቸውን ፡ እያረጋገጡ ፡ ወዲያው ፡
የሙሐመድን ፡ ሃይማኖት ፡ አቅፈው ፡ ተቀበሉ ። እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ የቱርኮች ፡
መንግሥት ፡ የሳራሴኖችን ፡ መንግሥት ፡ ወራሽ ፡ ሆነ ። ቀጥሎም ፡ ትንሽ ፡ እስ
ያን ፤ ሶርያን ፤ ሌሎችንም ፡ የእስያ ፡ ክፍል ፤ የሆኑትን ፡ አገሮች ፡ ቀድሞ ፡ የሳ
ራሴን ፡ መንግሥት ፡ ተግሪክ ፡ ጋር ፡ እየተዋጋ ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ የያዛቸውንም ፡
አገሮች ፡ ሁሉ ፡ ተራሱ ፡ ግዛት ፡ ጋር ፡ አቀላቅሎ ፡ ያዛቸው ።

፭ ፤ እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ ተቋቁሞ ፡ የነበረ ፡ የቱርክ ፡ መንግሥት ፡ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡
በኋላ ፡ ራሳቸውን ፡ ኦቶማኖች ፡ የሚያሰኙ ፡ ሌሎች ፡ የቱርክ ፡ ነገዶች ፡ ተነሥ
ተው ፡ ገለበጡት ፤ እነዚህም ፡ ከምሥራቅ ፡ ተካስፒያን ፡ ባሕር ፡ አውራጃ ፡ ካለው ፡
አገር ፡ የመጡ ፡ ናቸው ። አሁን ፡ ያለውን ፡ የኦቶማንን ፡ መንግሥት ፡ የመሠረቱ ፡
እነዚህ ፡ ናቸው ። ይህም ፡ የሆነ ፡ ባ፲፪፻፺፱ ፡ ዓ. ም. ነው ፤ መንግሥቱንም ፡ የመ
ሠረተው ፡ ኦቶማን ፡ አንደኛ ፡ ይባላል ።

፮ ፤ ቀድሞ ፡ ትንሽ ፡ እስያን ፡ የግሪክ ፡ መንግሥት ፡ ይዞት ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ሳራሴ
ኖች ፡ ወሰዱት ። ቀጥለው ፡ በኋላ ፡ ቱርኮች ፡ ወሰዱት ፡ ኦቶማን ፡ አገሩን ፡ ሲይ
ዘው ፡ ግሪክን ፡ ጨምሮ ፡ የኤውሮጳ ፡ ቱርክ ፡ እየተባለ ፡ ከሁኑ ፡ ጥቂት ፡ ይሰፋ፤
ነበር ።

፯ ፤ የዛሬው ፡ የቱርክ ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ቍስጥንጥንያ ፡ የተባለው ፡ ቀድሞ ፡ ቢዛን
ቲውም ፡ ይባል ፡ ነበር ። ይህም ፡ የተባለበት ፡ ምክንያት ፡ ቀድሞ ፡ በ፮፻፶፰ ፡ ከክ
ርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ቤዛስ ፡ የተባለ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ መሠረተው ፡ ነው ። ይኸውም ።
ከተማ ፡ በቀድሞ ፡ ግሪክ ፡ ዘመን ፡ እጅግ ፡ የገነነ ፡ ከተማ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። በዙ
ሪያው ፡ ያሉት ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ ለግሪክና ፡ ለሌሎች ፡ ነገዶች ፡ የቅኝ ፡ አገ
ሮች ፡ እየሆኑ ፡ ተገዝተዋል ። በኋላ ፡ ሮማውያን ፡ ተዋግተው ፡ ድል ፡ አደረ
ጉና ፡ ቢዛንቲውም ፡ የተባለው ፡ ስም ፡ ተለውጦ ። በ፫፻፴ ፡ ዓ. ም. ከክርስ
ቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡ ቍስጥንጥንያ ፡ ብሎ ፡ ሰየመው ።

፰ ፤ ቀድሞ ፡ ተበላሽቶ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ ነፍስ ፡ ዘርቶአል ። ቈስጠንጢኖ
ስም ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱንና ፡ አደባባዩን ፡ ከዚህ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ስለ ፡ አዛወረ ፡
ቍስጥንጥንያ ፡ የሮማውያን ፡ መንግሥት ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ሆነ ፤ በ፫፻፺፭ ፡ ዓ. ም.
የሮም ፡ መንግሥት ፡ የምሥራቅና ፡ የምዕራብ ፡ መንግሥት ፡ ተብሎ ፤ ከሁለት ፡
በተከፈለ ፡ ጊዜ ፡ እንደምታውቁት ፤ መቸውንም ፡ የቀድሞ ፡ የግሪክ ፡ መንግ
ሥት ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ይባል ፡ ነበር ።

፱ ፤ እንዲሁ ፡ እየተለዋወጠ ፡ አሁንም ፡ እስከምተርክላችሁ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ቈየ ።
እንደ ፡ ነገርኋችሁ ፡ ወደ ፡ መፍረስ ፡ አፋፍ ፡ ተቃረበ ። አስቀድሞ ፡ በትንሽ ፡ እስያ ፡
ተመሥርተው ፡ የነበሩ ፡ አሁንም ፡ ቀድሞ ፡ የሳራሴን ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡
የነበረውን ፡ ሁሉ ፡ ዋና ፡ አድርገው ፡ ይዘው  የነበሩ ፡ ኦቶማኖች ፡ በኤውሮጳ ፡
ባለው ፤ በግሪክ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ እጃቸውን ፡ ለመጫን ፡ የናፍቆት ፡ ዐይን ፡
ጣሉበት ።

፲ ፤ በዚሁ ፡ ዘመን ፡ የነበረው ፡ ሡልጣን ፡ ባጃዜት ፡ ይባላል ። እርሱም ፡ በ፲፫፻
፹፱ ፡ ዓ. ም. ነገሠ ፤ በሄደበት ፡ ሁሉ ፡ ድል ፡ አድራጊ ፡ ስለመሆኑ ፡ ስሙ ፡ ጥሩ ፡
ነበር ፤ ቱርኮች ፡ ኤልዴሪም ፡ ይሉታል ፡ መብረቅ ፡ ማለት ፡ ነው ።

፲፩ ፤ ይህም ፡ ቍስጥንጥንያን ፡ ለመውረር ፡ ሲሰናዳ ፡ ከርሱ ፡ የበለጠ ፡ ጀግና ፡
ከታርታር ፡ መጣና ፡ አስገበረው ። ይህንንም ፡ ታሜርሌን ፡ ይሉታል ። ወይም ፡
ቲሙር ፡ የታርታሩ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ አንካሳው ፡ ቲሙር ፡ ይሉት ፡
ነበር ። ታላቅ ፡ ውጊት ፡ አደረገና ፡ ባጃዜትን ፡ ድል ፡ አደረገው ። በዚህም ፡
ጦርነት ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ወታደሮች ፡ በውጊያው ፤ ወድቀዋል ።

፲፪ ፤ አንካሳው ፡ ቲሙር ፡ ቱርኮች ፡ ስለ ፡ ጀግንነቱ ፡ መብረቅ ፡ የሚሉትን ፡ ባጃ
ዜትን ፡ ማረከና ፡ በብረት ፡ ቀፎ ፡ ውስጥ ፡ አገብቶ ፡ እያዞረ ፡ እንደ ፡ አውሬ ፡
ለሕዝብ ፡ አሳየው ። ብዙች ፡ ድል ፡ አድራጎች ፡ በአውሬ ፡ ይመስላሉና ፡ እን
ዲሁ ፡ በብረት ፡ ቀፎ ፡ ውስጥ ፡ ተጠብቀው ፡ ቢኖሩ ፡ መልካም ፡ ነበር ።

፲፫ ፤ ቱርኮች ፡ የምሥራቅ ፤ ሮምን ፡ መንግሥት ፡ ወግተው ፡ ድል ፡ እንዳያደርጉ ፡
የባጃዜት ፡ ዕድል ፡ ማጣትና ፡ መዋረድ ፡ መሰናክል ፤ ሆነባቸው ። ስለ ፡ ሆነ ፡ በ፲
፬፻፶፫ ፡ ዓ. ም. ታላቁ ፡ ሙሐመድ ፡ በነገሠ ፡ ጊዜ ፡ ቍስጥንጥንያን ፡ እጅ ፤ አደ
ረጉ ፤ ንጉሡም ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡ እዚያው ፡ ላይ ፡ ሞተ ። ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀም
ረው ፡ ወደፊት ፡ ቱርኮች ፡ ምን ፡ አለብን ፡ ብለው ፡ በኤውሮጳ ፡ ያለ ፡ አሳብ ፡ ተን
ዘራፍጠው ፡ ተቀመጡ ። የያዙትም ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ቱርክ ፡ ተባለ ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ሳራሴን ፡ እንደምን ፡ ሆኑ ፡ ? የሳራሴን ፡ መንግሥት ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ተመ
ሠረተ ፡ ? የመሠረተውስ ፡ ማነው ፡ ?

፪ ፤ ካሊፎች ፡ የተባሉ ፡ ምንድናቸው ፡ ? ባግዳድ ፡ ከቍስጥንጥንያ ፡
ወዴት ፡ ነው ፡ ?

የካሊፎች ፡ ግዛት ፡ የት ፡ ድረስ ፡ ነው ፡ ?

፫ ፤ ቱርኮች ፡ የተባሉ ፡ እነማኔቸው ፡ ? መኖሪያቸው ፡ ወዴት ፡ ነበር ፡ ? በባግዳድ ፡ የሚኖሩ ፡ ካሊፎች ፡ ስለምን ፡ ያስሩዋቸዋል ፡ ?

፬ ፤ ቱርኮች ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ? የቱርክ ፡ መንግሥት ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፭ ፤ የቀድሞውን ፡ የቱርክን ፡ ግዛት ፡ የገለበጠው ፡ ማነው ፡ ? የኦቶማን ፡ መንግሥት ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ተመሠረተ ፡ ?

የመሠረተው ፡ ማነው ፡ ?

፮ ፤ ቀድሞ ፡ የግሪክ ፡ መንግሥት ፡ ጨምሮ ፡ ይዞት ፡ የነበረው ፡ አገር ፡ ማነው ፡ ?

በ፲፪፻፶፬ ፡ ደግሞ ፡ የትኛውን ፡ አገር ፡ ጨመረ ፡ ?

፯ ፤ ቍስጥንጥንያ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? የመሠረተው ፡ ማነው ፡ ? ምን ፡ ጊዜ ፡ ተመሠረተ ፡ ?

በጥንት ፡ ግሪኮች ፡ ዘመን ፡ እንዴት ፡ ነበር ፡ ? ስሙ ፡ የተለወጠው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?

ቢዛንቲውም ፡ ቍስጥንጥንያ ፡ ተብሎ ፡ የተሰየመው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?

የሰየመውስ ፡ ማነው ፡ ?

፰ ፤ የሮም ፡ መንግሥት ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? በ፫፻፺፭ ፡ ምን ፡ ተደረገ ፡ ? የግሪክ ፡ መንግሥት ፡ ምን ፡ ተባለ ፡ ?

ለሮም ፡ ምሥራቅ ፡ መንግሥት ፡ የተጨመሩ ፡ አገሮች ፡ የትኞች ፡ ናቸው ፡ ?

መልስ ፡ ግሪክ ፤ መቄዶንያ ፤ አሁን ፡ ቱርክ ፡ የሚባለው ፡ ትንሽ ፡ እስያ ፤ በዙሪያው ፡ ያሉ ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ ናቸው ።

፱ ፤ ኦቶማን ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፲ ፤ ባጃዜት ፡ የተባለ ፡ ማነው ፡ ? የነገሠውስ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?

ቱርኮች ፡ ማን ፡ ይሉታል ፡ ?

፲፩ ፤ ታሜርሊን ፡ የተባለ ፡ ማነው ፡ ?

፲፪ ፤ ቲሙር ፡ ባጃዜትን ፡ እንደምን ፡ አደረገው ፡ ? አሸናፊዎቹ ፡ እንደምን ፡ ሆኑ ፡ ?

፲፫ ፤ በ፲፬፻፶፫ ፤ ዓ. ም. ምን ፡ ተደረገ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፪ኛ ፡ ኤውሮጳ ።

### የቱርክ ፡ ታሪክ ፡ መከናወን ።

፩ ፤ ከቱርኮች ፡ ሡልጣኖች ፡ (ነገሥታት ፡) የሚበዙት ፡ አገዛዛቸው ፡ በደልና ፡ ደም ፡ ማፍሰስ ፡ የመላበት ፡ ነው ፡ በ፲፭፻፲፪ ፡ የነገሠው ፡ ሡልጣን ፡ ሴሊም ፡ ግብፅን ፡ ከበበና ፡ ድል ፡ አደረጋት ፤ የግብፅ ፡ ወታደሮች ፡ ማሜሊክስ ፡ ይባላሉ ። ስለነርሱም ፡ የግብፅን ፡ ታሪክ ፡ በተናገርሁ ፡ ጊዜ ፡ ነግሬያችኋለሁ ። ከነርሱም ፡ ብዙ ፡ ሺሕ ፡ የሚሆኑት ፡ ተማረኩ ።

፪ ፤ ከድሉ ፡ በኋላ ፡ በነጭ ፡ ዐባይ ፡ ወንዝ ፡ ዳርና ፡ በካይሮ ፡ በር፡ አጠገብ ያጌጠና፡ የደመቀው ፡ ዙፋኑ ፡ እንዲቆም ፡ ሡልጣኑ ፡ አዘዘ ። በዚያ ፡ በዙፋኑ ፡ ተቀምጦ ፡ እየተመለከተ ፡ ማምሉክስ ፡ የተባሉት ፡ የግብፅ ፡ ምርኮኞች ፡ ሁሉ ፡ እሬቱ፡እየታ ረዱ ፡ ወደ ፡ ነጭ ፡ ዐባይ ፡ እንዲጣሉ ፡ አዘዘ ።

፫ ፤ በ፲፭፻፺፭ ፡ የነገሠ ፡ ፫ኛ ፡ ሙሐመድ ፡ ዐሥራ ፡ ዘጠኝ ፡ ወንድሞች ፡ ነበሩት፡ ዙፋኑን ፡ እንዳይቀሙት ፡ ስለ፡ፈራ፡እንደማይንቀሳቀሱ ፡ አድርጎ ፡ ሁሉንም፡ ጨቈ ናቸው ።

፬ ፤ በ፲፮፻፳፫ ፡ አሙራት ፡ አራተኛ ፡ የተባለ ፡ ነገሠ ። ይህም፡ሰውነተ፡ቢስ ፡ ዐሥራ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ሰው ፡ አሳርዷል ። ለርሱም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘው ፡ ጨዋታ ፡ ሠይ ፉን ፡ መዝዞ ፡ ሌሊት ፡ በዋናው ፡ጐዳና ፡ እየሮጠ ፡ በመንገድ፡ያገኘውን ፡ ሁሉ፡ ማንንም ፡ ቢሆን ፡ አንገቱን ፡ እየበጠሰ ፡ መሄድ ፡ ነበር ።

፭ ፤ ባንድ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ምክንያት ፡ የጭከና ፡ ሥራ ፡ ተሠርቶአል ። ይህም፡የሆ ነው ፡ ጃኒዛሪስ ፡ በሚባሉ ፡ ጭፍሮች ፡ ላይ ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ብዙ ፡ ነበሩ ፡ ሙሐ መድ ፡ ፩ኛ ፡ የተባለው፡በሺሕ፡ ፫፻ ፡ ዓ. ም. ያቆማቸው ፡ ነበሩ ። ብርቱ፡ ጭፍሮች ሆነው ፡ አያል ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ቈይተው ፡ ስለ ፡ በዙ ፡ የሡልጣን ፡ ዘበኞች ፡ ወይም ፡ ጠባቆች ፡ ይባላሉ ። እያደር ፡ ኀይላቸው ፡ እየበዛ ፡ ጕልበት ፡ ተሰማቸ ውና ፡ በመንግሥቱ ፡ ካሉት ፡ የጦር ፡ ወታደሮች ፡ ይልቅ ፡ እነዚህ ፡ ኀይለኞች፡ ሁነው ፡ እምቢተኞችና ፡ የሚያስፈሩ ፡ ዐመፀኞች ፡ ሆኑ ።

፮ ፤ ስለዚህ ፡ ንጉሡ ፡ ሙሐመድ ፡ ከነርሱ ፡ ሥልጣን ፡ ነፃ ፡ ለመውጣት ፡ ፈልጎ ፡ በ፲፰፻፳፮ ፡ ዓ. ም. ጃኒዛሪስን ፡ እንዲከቡ ፡ የቀሩት ፡ ጭፍሮቹን ፡ አዘዘ ፡ እንዲ ሁም ፡ ተደረገና ፡ ሁሉንም ፡ አንድ፡ሳይቀር፡ያለምሕረት፡በጥይት፡አስፈጃቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሡልጣኑ ፡ የቱርክን ፡ ልማድ ፡ ለማደስና ፡ የኤውሮጳውያንን፡ ሥል ጣኔ ፡ እንዲቀበሉ ፡ ለማድረግ ፡ ሞከረ ። ካሰበውም ፡ ጥቂት ፡ እንጂ ፡ ብዙ ፡ ለማ ድረግ ፡ አልቻለም ። እንዳሰበው ፡ ሳይሆንለት ፡ በ፲፰፻፴፱ ፡ ሞተና ፡ መንግሥቱን፡ ልጁ ፡ አብዱል ፡ሜጂድ ፡ ወረሰው ። ይህም፡ሰኔ ፡ ፳፭ ፡ ቀን ፡ ፲፰፻፷፩ ፡ ሞተ ። በ፲፰፻፶፫፡፶፬—፶፮ ፡ ከመስኮብ ፡ ጋር ፡ ጦርነት ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ፡ቱርክ፡ የጦር ፡ጓደ ኞቹን ፡ ፈረንሳይንና ፡ እንግሊዝን ፡ ለመርዳት ፡ ከመቶ ፡ ሺሕ፡የሚበልጥ፡ወታደር፡ አቀረበ ።

፯ ፤ የአብዱል ፡ ሜጂድን ፡ ዙፋን ፡ አብዱል ፡ አዚዝ ፡ ወረሰ ። ይህም ፡ ሥልጣን ፡ ፲፰፻፸፮ ፤ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ነገሠ ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ተሻረና ፡ ያጐቱ፡ልጅ፡ሙራድ፡ አምስተኛ ፡ ስፍራሙን ፡ ወሰደ ። እሱም፡አእምሮው ፡ በሽተኛ ፡ ስለ፡ሆነ ፡ ጥቂት ፡ ወራቶች ፡ ነገሠና ፡ ወንድሙ ፡ አብዱል ፡ አሚድ ፡ ሁለተኛ ፡ ነገሠ ። በ፲፰፻፸፯ ፡ መስኮብ ፡ ቱርክን ፡ ወረረውና ፡ ባያለበት ፡ ጦርነት ፡ ሆነ ። የኤውሮጳም ፡ መንግ ሥታት ፡ በነገሩ ፡ ገቡበትና ፡ ዕርቅና ፡ ሰላም ፡ ወረደ ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ የቱርክ ፡ ሡልጣኖች ፡ መንግሥ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ሡልጣን ፡ ሴሊም ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ሚምሉክስ ፡ የተባሉት ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?

፪ ፤ ሡጣልን ፡ ምን ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ።

፫ ፡ ሦስተኛው ፡ ሙሐመድ ፡ የነገሠው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ? የክፋት ፡ ሥራ ፡ የሠራው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?

፬ ፤ በ፲፯፻፳፩ ፡ ሡልጣን ፡ የሆነው ፡ ማነው ፡ ? አሙራት ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፭ ፤ ባኒዛሪስ ፡ የተባሉ ፡ እነማናቸው ፡ ? ምን ፡ ጊዜ ፡ ተመሠረቱ ፡ ?

፮ ፤ በ፲፰፻፳፯ ፡ ምን ፡ ተደረገ ፡ ? ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ሡልጣን ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ? መንግሥቱን ፡ ማን ፡ ወረሰው ፡ ? አብዱል ፡ ሚጂድን ፡ ማን ፡ ወረሰው ፡ ? ስለምን ፡ ሙራድ ፡ ፭ኛ ፡ የተባለው ፡ ተሻረ ፡ ?

፯ ፤ የዛሬው ፡ ሡልጣን ፡ ማን ፡ ይባላል ፡ ?

## ምዕራፍ ፤ ፱፳፪ ፤ ኤውሮጳ ።

### የጥንት ፤ የእስጳንያ ፤ ታሪክና ፤

### ሙሪሽ ፤ የተባሉ ፤ ነገድ ፤ ድል ፤ እንዳገኙ ።

፩ ፤ የእስጳንያ ፤ ግዛት ፤ ከፈረንሳይ ፤ የሚለይበት ፤ ፒሪኒር ፤ በሚባል ፤ ተራራ ፤ ነው ። በምዕራብ ፤ ፖርቱጋል ፤ ነው ፤ ባንድ ፤ ወገን ፤ የአትላንቲክ ፤ ውቅያኖስ ፤ የቢስኪ ፤ ጠረፍና ፤ የሜዴቴራኒያን ፤ ባሕር ፤ ነው ። እስጳንያ ፤ አገሩ ፤ በሁለት ፤ ባሕሮች ፤ መኻከል ፤ ሆኖ ፤ በሰፊው ፤ የተዘረጋ ፤ የብስ ፤ ነው ።

፪ ፤ እስጳንያ ፤ በጣም ፤ የታወቀ ፤ ስመ ፤ ጥሩ ፤ አገር ፤ ነው ። አገሩ ፤ አውሬ ፤ የመ ላበትና ፤ ተራራ ፤ የበዛበት ፤ ሆኖ ፤ በመኻከሉ ፤ እጅግ ፤ ያማሩ ፤ ረባዳ ፤ አገሮች ፤ አሉበት ፤ አየሩ ፤ ሙቀት ፤ ሳለ ፤ እጅግ ፤ ደስ ፤ የሚያሰኝ ፤ ነው ። ወይንና ፤ ወይራ ፤ ሎሚ ፤ አልሞንድ ፤ በለስ ፤ ሲትሮንና ፤ ፓሜግራሜንት ፤ ያበቅላል ።

፫ ፤ እስጳንያ ፤ ጥሩ ፤ ፈረስ ፤ የሚረባበት ፤ አገር ፤ መሆኑ ፤ በጣም ፤ የታወቀ ፤ ነው ። ደግሞ ፤ ሜሪኖ ፤ የሚሉት ፤ በግ ፤ መጀመሪያ ፤ የተገኘው ፤ በዚሁ ፤ አገር ፤ ነው ። የዚሁ ፤ ዐይነት ፤ በግ ፤ በብዙ ፤ የሚገኘው ፤ በአሜሪካ ፤ ነው ። ዛሬ ፤ ግን ፤ በዓለሙ ፤ ሁሉ ፤ ይገኛል ። መጀመሪያ ፤ በዓለም ፤ ጥሩ ፤ የበግ ፤ ጠጕር ፤ የተገኘው ፤ ከነዚህ ፤ ዐይነት ፤ በጎች ፤ ነው

፬ ፤ እስጳንያ ፤ ፲፮ ፤ ሚሊዮን ፤ ያህል ፤ ባላገሮች ፤ አሉዋት ። ሕዝቡ ፤ በጠቅላላው ፤ እምብዛም ፤ ዕውቀት ፤ የላቸውም ። ደግሞም ፤ አምልኮ ፤ ባዕድ ፤ ይወዳሉ ። ነገር ፤ ግን ፤ ቁምነገራሞች ፤ ለምምነትና ፤ የለዘበ ፤ ጠባይ ፤ ያላቸው ፤ ይመስላሉ ። ከሜዳ ፤ ወጥተው ፤ በደስታ ፤ መዝፈንና ፤ መጨፈር ፤ ይወዳሉ ።

፭ ፤ የእስጳንያ ፤ ዋና ፤ ከተማ ፤ ማድሪድ ፤ እጅግ ፤ ያማረች ፤ ከተማ ፤ ናት ። ሙር ፤ የተ ባሉት ፤ ነገድ ፤ የሠሩዋቸው ፤ ታላላቅ ፤ ቤቶችና ፤ ቤተ ፤ ክርስቲያኖች ፤ ቤተ ፤ መንግ ሥቶችም ፤ በእስጳንያ ፤ ይገኛሉ ። ታሪካቸውንም ፤ አሁን ፤ እነግራችኋለሁ ። የነዚ ህም ፤ ሕንፃዎች ፤ ሥራ ፤ እጅግ ፤ የሚያስደንቅ ፤ ተብሎ ፤ በዓለም ፤ የታወቀ ፤ ነው ። በማነኛውም ፤ ሁኔታው ፤ ፈጽሞ ፤ የጥንት ፤ የግሪክንና ፤ የሮምን ፤ ሥራ ፤ አይመ ስልም ። ይህም ፤ የጥንት ፤ የጎቶችን ፤ ሥራ ፤ ይመስላል ።

፮ ፤ ጊዜና ፤ ስፍራ ፤ ባገኝ ፤ ስለ ፤ እስጳንያ ፤ ረጅም ፤ ታሪክ ፤ በብዙ ፤ አድርጌ ፤ በነገርኋችሁ ፤ ነበር ። ዳሩ ፤ ግን ፤ የዚህን ፤ ሐተታ ፤ በሌላው ፤ መጽሐፍ ፤ እተርክ ላችኋለሁ ፤ በማለት ፤ ታሪኩን ፤ በዚህ ፤ አሳጥሬዋለሁ ።

፯ ፤ ፊኒቅያኖች ፤ በባሕር ፤ አድርገው ፤ ወደዚህ ፤ እስኪመጡ ፤ ድረስ ፤ ስለ ፤ እስጳንያ ፤ ታሪክ ፤ የታወቀው ፤ እጅግ ፤ ጥቂት ፤ ነው ። ፊኒቅያ ፤ ማለት ፤ እን ደምታውቁት ፤ ለከንዓን ፤ የቀረበ ፤ አገር ፤ ነው ። ሁለት ፤ ሺሕ ፤ ማይል ፤ ርቀት ፤ ያለው ፤ ነው ። ከዚህ ፤ መጥተው ፤ በጊብራልታር ፤ በር ፤ ሁለት ፤ ሐውልት ፤ አቆሙ ።

እነዚህንም ፡ ሐውልቶች ፡ የሔርኩሎስ ፡ ምሰሶዎች ፡ አሉዋቸው ። የጥንት ፡ ሰዎች ፡ እነዚህን ፡ ምሰሶዎች ፡ አልፈው ፡ ወደ ፡ አትላንቲክ ፡ ውቅያኖስ ፡ ለመንዝ ፡ አይዳፈሩም ፡ ነበር ።

፰ ፤ ግሪኮች ፡ በእስጳንያ ፡ አያሉች ፡ ከተሞች ፡ መሥርተዋል ። በኋላ ፡ ግን ፡ ካርታጎች ፡ አገሩን ፡ እጅ ፡ አደረጉት ። ነገር ፡ ግን ፡ በ፪፻፴፮ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ሮማውያን ፡ ወሰዱትና ፡ እስከ ፡ ፬፻፲፮ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ እንደያዙት ፡ ቈዩ ። ከዚህ ፡ ወዲያ ፡ እስጳንያ ፡ ሱቪ ፤ አላንስ ፤ ቫንዳልስ ፡ በሚባሉ ፡ ከሰሜን ፡ ወገን ፡ በመጡ ፡ በአራዊት ፡ ሕዝብ ፡ ተወረረች ።

፱ ፤ ከነዚህም ፡ አራዊት ፡ አያሌዎቹ ፡ ባገሪቱ ፡ ውስጥ ፡ ከመቶ ፡ ዓመት ፡ የሚበልጥ ፡ ተቀምጠው ፡ ኖሩ ። ከዚህ ፡ ወዲያ ፡ ጎቶች ፡ ወይም ፡ ቪስጎቶች ፡ የሚባሉ ፡ ሌሎች ፡ አራዊት ፡ ሕዝብ ፡ መጡና ፡ እነዚህን ፡ ካሉበት ፡ አስወጥተው ፡ በመላው ፡ እስጳንያ ፡ ተናኙበት ። እነዚህም ፡ በአገሩ ፡ ተቀመጡበትና ፡ በኋላ ፡ መንግሥት ፡ መሠረቱ ።

፲ ፤ ጎቶች ፡ በእስጳንያ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ከኖሩ ፡ በኋላ ፡ ሮዴሪክ ፡ የተባለ ፡ ንጉሥ ፡ አነገሡ ። ንጉሡም ፡ በጎቶችና ፡ በእስጳኞች ፡ መካከል ፡ ተከብሮ ፡ የሚኖረውን ፡ ኀይለኛውን ፡ ካውንት ፡ ጁሊያን ፡ የተባለውን ፡ ጀግና ፡ በሚያሳዝን ፡ ነገር ፡ ጎዳው ፡ ጁሊያንም ፡ ይህንኑ ፡ እበቀላለሁ ፡ ሲል ፡ አገሩ ፡ የሚጎዳበት ፡ ሆነ ።

፲፩ ፤ ፊት ፡ እንደተናገርሁት ፡ በሞሪታኒያ ፤ ከእስጳንያ ፡ በማይርቅ ፡ በአፍሪካ ፡ ሰሜን ፡ ጠረፍ ፡ ሳራሴን ፡ የተባሉ ፡ አንድ ፡ ነገድ ፡ ነበሩ ። እነዚህም ፡ ሞሪ ፡ ወይም ፡ ሙር ፡ ይባላሉ ። እነዚህም ፡ ባሕርን ፡ ተሻግረው ፡ እስጳንያን ፡ እንዲወሩ ፡ ከሚኖሩበት ፡ አገር ፡ ካውንት ፡ ጁሊያን ፡ ጠራቸው ።

፲፪ ፤ እንዲሁም ፡ እነዚህ ፡ አረማውያን ፡ ታሪፍ ፡ በተባለ ፡ ጀኔራላቸው ፡ እየተመሩ ፡ ባሕርን ፡ ተሻግረው ፡ ወደ ፡ እስጳንያ ፡ ጠረፍ ፡ ደረሱ ። የጎቶች ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ ንጉሥ ፡ ሮዴሪክ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ሰበሰበና ፡ በእስጳንያ ፡ ደቡብ ፡ ዜርስ ፡ በሚባል ፡ ስፍራ ፡ ተገናኝተው ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ውጊት ፡ ተዋጉ ።

፲፫ ፤ ሙሮች ፡ ፈጽመው ፡ ድል ፡ አደረጓቸው ። ንጉሡ ፡ ሮዴሪክ ፡ የደረሰበት ፡ ከቶ ፡ አልታወቀም ። ፈረሱና ፡ ጦሩ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ የሚደፋው ፡ የራስ ፡ ቁር ፤ ጋሻውና ፡ በደረቱ ፡ ላይ ፡ የሚለብሰው ፡ የብረት ፡ ልብስ ፤ ከተዋጉበት ፡ ስፍራ ፡ አጠገብ ፡ ባለው ፡ ወንዝ ፡ ዳር ፡ ወድቆ ፡ ተገኘ ። ሰውነቱ ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ ተገኘ ፡ አልተባለም ። ይህም ፡ የሆነ ፡ በ፯፻፲፩ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ ነው ።

፲፬ ፤ እስጳንያዎች ፡ ግን ፡ ንጉሥ ፡ ሮዴሪክ ፡ በሕይወት ፡ አለ ፡ ወደፊት ፡ መጥቶ ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱን ፡ ይዞ ፡ ሙሮችን ፡ ወግቶ ፡ ያስወጣቸዋል ፡ ብለው ፡ ያምናሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ የርሱ ፡ ጦር ፡ ድምጽም ፡ ዳግመኛ ፡ አልተሰማም ። የጎቶች ፡ ጊዜ ፡ በመውደቁ ፡ ተበላሽቶ ፡ ስለ ፡ ቀረ ፡ የጎቶች ፡ መጨረሻ ፡ ሮዴሪክ ፡ ተባለ ።

፲፭ ፤ የንጉሥ ፡ ተወላጅነት ፡ ያለው ፡ ፒላጆ ፡ የተባለ ፡ ሙሮች ፡ ሳይገድሉዋቸው ፡ የቀሩትን ፡ የእስጳንያ ፡ ጎቶች ፡ የተባሉትን ፡ ሰብስቦ ፡ ዋና ፡ መሪ ፡ ሆነና ፡ እስቱሪያ

ስና ፡ ቡርጎ ፡ ወደ ፡ ተባሉ ፡ ተራሮች ፡ ይዘዋቸው ፡ ሄዱ ። በዚያም ፡ ትንሽ ፡ መንግ ሥት ፡ መሠረተ ። ሙሮች ፡ በእስጳንያ ፡ ውስጥ ፡ ያልነኩትና ፡ ድል ፡ ያላደረጉት ፡ ይህንኑ ፡ መንግሥት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

፲፯ ፤ የፒላጂዎ ፡ ተከታዮች ፡ የመንግሥታቸውን ፡ ዳርቻ ፡ ሲያስፋፉት ፡ ሙሮችም ፡ ከእ ስጳንያ ፡ ሦስቱን ፡ እጅ ፡ እንደያዙ ፡ ቈዩ ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ እስጳንያ ፡ ያለው ፡ ከኤውሮጳ ፡ በወዴት ፡ በኩል ፡ ነው ፡ ?
በእስጳንያና ፡ በዩናይትድ ፡ እስቴትስ ፡ መኻከል ፡ ያለው ፡ ውቅያኖስ ፡ ማን ፡ ይባላል ፡ ?

፪ ፤ እስጳንያ ፡ ከፈረንሳይ ፡ በምን ፡ ይለያያል ፡ ? የእስጳንያ ፡ ዳርቻ ፡ የት ፡ ድረስ ፡ ነው ፡ ? እስጳንያ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ አገር ፡ ነው ፡ ? አየሩ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? ምን ፡ ያፈራል ፡ ? ወደ ፡ እስጳንያ ፡ ሄዳችሁ ፡ ከሚያምረው ፡ ፍሬ ፡ መብ ላት ፡ ትወዳላችሁን ፡ ?

፫ ፤ የእስጳንያ ፡ ፈረሶች ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ? ሚሪኖ ፡ የሚባሉ ፡ በጎችሳ ፡ ?

፬ ፤ የሕዝቡ ፡ ብዛት ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? ሕዝቡ ፡ እንደምን ፡ ናቸው ፡ ?
ዋናው ፡ ከተማ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ? ማድሪድ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ከተማ ፡ ነው ? ፡
ማድሪድ ፡ ከናንተ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ? ከሎንዶን ፤ ከፓሪስ ፡ ? ከሮም ፤ ከአልጀር ፡ ?

፭ ፤ በእስጳንያ ፡ ሙሮች ፡ (ሞሮክ) የሠሯቸው ፡ ሕንፃዎች ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ? የእስጳንያ ፡ የቀድሞ ፡ ታሪክ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? ፊኒቂያ ፡ በየት ፡ በኩል ፡ ነው ፡ ? ከእስጳንያ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ይርቃል ፡ ? ፊኒቂያኖች ፡ በእስጳንያ ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ? የሜዲቴራንያን ፡ ባሕር ፡ ከአትላንቲክ ፡ ውቅያኖስ ፡ ጋር ፡ በየት ፡ ይጋጠማል? የሔርኩሊስ ፡ ዐምዶች ፡ የቆሙት ፡ የት ፡ ላይ ፡ ነበር ፡ ? የጥንት ፡ ሰዎች በመርከብ ፡ እየተቀመጡ ፡ የት ፡ ድረስ ፡ ይሄዱ ፡ ነበር ፡ ?

፮ ፤ ግሪኮች ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ? ካርታጎችና ፡ ሮማዊያን ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ? እስጳንያዎችን ፡ ያሸነፉ ፡ የወዴት ፡ አራዊት ፡ ሕዝብ ናቸው ፡ ? እስጳ ንያን ፡ ድል ፡ ያደረጉት ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
ሱቪርና ፡ ሌሎችም ፡ አራዊት ፡ ሕዝብ] በእስጳንያ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ዘመን ፡ ቈዩ ፡ ?

፯ ፤ እነዚህኑ ፡ ሱቪርና ፡ አራዊት ፡ ሕዝብ ፡ ከገሩ ፡ ውስጥ ፡ ያስወጣቸው ፡ ማነው ፡ ? ጎቶች ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?

፲ ፤ ሮዲሪክ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ካውንት ፡ ጁሊያን ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ?

፲፩ ፤ ሞሪታኒያ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ከእስጳንያ ፡ ወዴት ፡ ነው ? ፡
ካውንት ፡ ጁሊያን ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ምን ፡ አደረገ ፡ ?

፲፪ ፤ ሙሮች ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ? ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ምን ፡ ተከተለ ፡ ?
፲፫ ፤ የንጉሥ ፡ ሮዴሪክ ፡ ፍጻሜ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ይህ ፡ የሆነው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
፲፬ ፤ እስጳኞች ፡ ምን ፡ ያምኑ ፡ ነበር ፡ ? ስለምን ፡ ሮዴሪክ ፡ የጎቶች ፡ መጨረሻ ፡ ተባለ ፡ ?
፲፭ ፡ ፒላጂዎ ፡ እንደምን ፡ ሆነ ፡ ? ሙሮች ፡ ያልደረሱበት ፡ የእስጳንያ ፡ ክፍል ፡ የቱ ፡ ነው ፡ ?
፲፮ ፤ የፒላጂዎ ፡ ወራሽ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
ሙሮች ፡ ረጅም ፡ (ወራት ፡ ) ዘመን ፡ ይዘውት ፡ የነበረ ፡ የእስጳንያ ፡ ክፍል ፡ የትኛው ፡ ነው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፲፰፫ ፡ ኤውሮጳ ።

### በሙሮችና ፡ በእስጳንያዎች ፡ መኻከል ፡ ስለ ፡ ተደረገው ፡ ጦርነት ።

፩ ፤ መጀመሪያ ፡ ሙሮች ፡ እስጳንያን ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ አራዊት ፡ ያሉ ፡ ሕዝብ ፡ ነበሩ ። ነገር ፡ ግን ፡ ቶሎ ብለው ፡ ሠለጠኑና ፡ እጅግ የለዘቡ ፡ ሕዝብ ፡ ሆኑ ። በኤውሮጳ ፡ በማንኛውም ፡ ክፍል ፡ ከሚደረገው ፡ ይልቅ በነዚህ ፡ መኻከል ፡ ብርቱ ፡ ትምህርት ፡ ነበር ።

፪ ፤ ጎርዶቫ ፡ በተባለው ፡ ከተማ ፡ ፫፻ ፡ ሺሕ ፡ መጻሕፍት ፡ ያሉበት ፡ ቤት ፡ ነበር ። ደግሞ ፡ ሙሮች ፡ በያዙት ፡ በእስጳንያ ፡ ግዛታቸው ፤ ውስጥ ፡ ፸ ፡ የሚሆኑ ፡ የሕዝብ ፡ የመጻሕፍት ፡ ቤቶች ፡ ነበሩ ። ሙሮች ፡ እጅግ ፡ አድርገው ፡ ቅኔና ፡ ሙዚቃ ፡ ይወዳሉ ።

፫ ፤ በእስጳንያ ፡ አያሎች ፡ ያማሩ ፡ ሕንፃዎችና ፡ ቤቶች ፡ ሠርተዋል ። አልሀምብራ ፡ የተባለው ፡ የግሬናዳ ፡ ከተማ ፡ የሙሮች ፡ ነገሥታት ፡ መኖሪያ ፡ ነው ። ከእብነ ፡ በረድ ፡ ተሠርቶ ፡ በተጠረበ ፡ ደንጊያ ፡ ያጌጠ ፡ ነው ። ሀሩር ፡ የሆነውን ፡ አገር ፡ ከእልፍኙና ፡ ካዳራሹ ፡ ደጅ ፡ እየዘለለ ፡ የሚረጨው ፡ ምንጭ ፡ ያበርደዋል ። የሙሮች ፡ ነገሥታት ፡ በዚህ ፡ እንዲቀበሩ ፡ ስለ ፡ ፈለጉ ፡ ከአልሀምብራ ፡ በታች ፡ ያስቆፈሩዋቸው ፡ ዋሻዎች ፡ (ሕንፃዎች) ፡ ነበሩ ። መቃብራቸውንና ፡ ቤተ ፡ መንግሥታቸውን ፡ በአልሀምብራ ፡ ማድረግ ፡ ይወዱ ፡ ነበር ።

፬ ፤ እስጳንያዎች ፡ ሙሮችን ፡ ጠልተው ፡ ነበሩና ፡ ሁልጊዜ ፡ ዕርቅ ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይዋጉ ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ ድሉ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ላንደኛው ፡ ወገን ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ለሌላው ፡ ወገን ፡ ይሆናል ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሲዋጉ ፡ ባንዱ ፡ ጦርነት ፡ ሰማኒያ ፡ ሺሕ ፡ ሙሮች ፡ ታረዱ ።

፭ ፤ ባንድ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ ከሙሮች ፡ ወገን ፡ የነበረ ፡ አልማንዞር ፡ የተባለ ፡ ጀግና ፡ እስጳኞችን ፡ ከአምሳ ፡ ጊዜ ፡ ይበልጥ ፡ እየመላለሰ ፡ ድል ፡ አድርጓቸዋል ፡ ይባላል ። ኮምፖሳቲላ ፡ የተባለች ፡ ከተማቸውን ፡ ያዛትና ፡ ከዚሁ ፡ ስፍራ ፡ የታላቁን ፡ ሕንፃ ፡ መዝጊያ ፡ በትከሻቸው ፡ ተሸክመው ፡ ወደ ፡ ኮርዶቫ ፡ እንዲያደርሱ ፡ ምርኮኞቹን ፡ በግድ ፡ አዘዛቸው ።

፮ ፤ ከነዚህ ፣ ወገን ፣ እጅግ ፣ ስመ ፣ ጥሩ ፣ ጀግና ፣ ተብሎ ፣ ተውስጣቸው ፣ ብቅ፣ ያለው ፣ ደን ፣ በድሪጎ ፣ ደቤቫር ፣ ነበር ። ጭማሪ ፣ ስሙ ፣ ሴድ ፣ ካምፔዶር ፣ ወይም ፣ ተወዳዳሪ ፣ ጓደኛ ፣ የሌለው ፣ ጌታ ፣ ማለት ፣ ነው ። እርሱም ፣ እየመላለሰ ፣ ሙሮችን ፣ ድል ፣ አድርጓል ። እስጳንያዎች ፣ መቸውንም ፣ ቢሆን ፣ ሴድ፣ ካምፔዶርን ፣ መሪ ፣ አድርገው ፣ በሄዱ ፣ ቍጥር ፣ ድል ፣ እንዲያገኙ ፣ አረጋግጠዋል ።

፯ ፤ ተወዳዳሪ ፣ የሌለው ፣ ጌታ ፣ በሞተ ፣ ጊዜ ፣ ሙሮች ፣ እንደ ፣ ገና ፣ ነፍስ ፣ ዘርተው ፣ ተንቀሳቀሱና ፣ እስጳንያዎችን ፣ ፊት ፣ ለፊት ፣ ገጠሙዋቸው ። ሴድ ፣ ካምፔዶር ፣ የተቀመጠባትን ፣ ከተማ ፣ ስለ ፣ ከበቡዋት ። እስጳንያዎችም ፣ ወጥተው፣ ገጠሙዋቸው ። ፊቱ ፣ የሞት ፣ መልክ ፣ የሚመስል ፣ የጦር ፣ መሪያቸው ፣ መሣሪያውን ፣ ታጥቆ ፣ እንደ ፣ ተሰለፈ ፣ በጦር ፣ ፊት ፣ በሰንጋ ፣ እያጋፈተ ፣ ቀረበ ።

፰ ፤ ሙሮች ይህን ፣ በተመለከቱ ፣ ጊዜ ፣ ይህማ ፣ ሴድ ፣ ካምፔዶር ፣ ነው ፣ እስጳኞች ፣ ከመቃብር ፣ አስነሥተው ፣ በፈረስ ፣ አስቀምጠውታል ። እነሆ ፣ በሕይወቱ ፣ ሳለ ፣ በሚጋልበው ፣ ፈረስ ፣ ተቀምጦ ፣ በሰልፍ ፣ ፊት ፣ እናየዋለን ፣ ብለው፣ ወደ ፣ ኋላቸው ፣ ሸሽት ፣ ጀመሩ ። እንደዚህ ፣ አድርጎ ፣ የሞተው ፣ ጀግና ፣ ድል ፣ አደረገ ።

፱ ፤ ስለ ፣ ሙሮችና ፣ ስለ ፣ እስጳኞች ፣ ጦርነት ፣ ልዩ ፣ ልዩ ፣ ታሪክ ፣ ይነገራል ። አንድ፣ ጊዜ ፣ እንዲህ ፣ ተብሎ ፣ ተወራ ፤ ለእስጳኞች ፣ መሪ ፣ ሆኖ ፣ በጦር ፣ ግንባር ፣ እንዲታይ ፣ አንድ ፣ ቅዱስ ፣ ከሰማይ ፣ ወረደ ። አንድ ፣ ጊዜ ፣ ደግሞ ፣ እስጳንያ ፣ ጠላቶቻቸውን ፣ አርደው ፣ እስኪጨረሱ ፣ ድረስ ፣ ጊዜ ፣ እንዲያገኙ ፣ ፀሓይ ፣ ቆመች ፤ አንድ ፣ ጊዜ ፣ ደግሞ ፣ የጦር ፣ ሠራዊታቸውን ፣ ለማበረታታት ፣ ሲሉ ፣ በሰማይ ፣ የሚያንጸባርቅ ፣ መስቀል ፣ ታይቶአል ፣ አስኝተዋል ።

፲ ፤ ዳሩ ፣ ግን ፣ ይህ ፣ ሁሉ ፣ ተረት ፣ ነበር ። ስለ ፣ ሆነ ፣ ሙሮች ፣ ተግሬናዳ ፣ በቀር፣ ሌላውን ፣ ከእስጳኞች ፣ የያዙትን ፣ ግዛታቸውን ፣ ሁሉ ፣ ማጣታቸው ፣ እርግጥ ፣ ነው ። ፌርዲናና ፣ ኢዛቤላ ፣ በነገሡ ፣ ጊዜ ፣ ፈጽመው ፣ ከእስጳንያ ፣ አስወጡዋቸው ። ይህም ፣ የሆነ ፣ በ፲፬፻፺፪ ፣ ዓ. ም. ቅርብ ፣ በስምንተኛው ፣ መቶ ፣ ዓመት ፣ የጎቶች ፣ ንጉሥ ፣ ሬዶሪክ ፣ ከጠፋ ፣ በኋላ ፣ ነው ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ስለ ፣ ሙሮች ፣ ምን ፣ ትላለህ ፣ ? በኮርዶቫ ፣ የነበሩ ፣ መጻሕፍት ፣ እንዴት ፣ ሆኑ ፣ ?

፪ ፤ በሌሎች ፣ ከተሞች ፣ የነበሩ ፣ መጻሕፍትስ ፣ ? ሙሮች ፣ ምን ፣ ይወዱ ፣ ነበር ፣ ?

፫ ፤ በእስጳንያ ፣ እንዴት ፣ ያለ ፣ ቤት ፣ ሠሩ ፣ ? ስለ ፣ አልሀምብራ ፣ ተናገር ። በአልሀምብራ ፣ በስተ ፣ ውስጥ ፣ ምን ፣ ነበር ፣ ?

፬ ፤ እስጳኞች ፣ በሙሮች ፣ ላይ ፣ ስሜታቸው ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ? ጦርነታቸው ፣ እንዴት ፣ ነበር ፣ ?

፭ ፤ አልማንዞር ፣ ማነው ፣ ? የትኛውን ፣ ከተማ ፣ ያዘባቸው ፣ ?
፮ ፤ እንዴት ፣ ያለ ፣ ጀግና ፣ እንደ ፣ ነበረ ፣ ታመለከታለህን ፣ ? ምን ፣ ሆነ ፣ ?
፯ ፤ እርሱ ፣ ከሞተ ፣ በኋላ ፣ ሙሮች ፣ ምን ፣ ሆኑ ፣ ? የእስጳኞች ፣ መሪ ፣ ማን ፣ ሆነ ፣ ?
፰ ፤ የሲድ ፣ ካምፒዶንን ፣ ሬሳ ፣ ባዩ ፣ ጊዜ ፣ ሙሮች ፣ ምን ፣ ሆኑ ፣ ?
፱ ፤ ስለ ፣ እስጳንያና ፣ ስለ ፣ ሙሮች ፣ ጦርነት ፣ ምን ፣ ይነገራል ፣ ?
፲ ፤ በመጨረሻው ፣ ለሙሮች ፣ ምን ፣ ቀረላቸው ፣ ?
ሙሮች ፣ ከእስጴን ፣ ተነድተው ፣ የወጡት ፣ ምን ፣ ጊዜ ፣ ነው ፣ ?

## ምዕራፍ ፣ ፻፳፱ ፣ ኤውሮጳ ።

### እስጳንያዎች ፣ ስለ ፣ ሃይማኖት ፣ ምርመራ ፣ እንደ ፣ አቆሙ ።

፩ ፤ በእስጳንያ ፣ የሃይማኖት ፣ ምርመራ ፣ በመቆሙ ፣ የፌርዴናንድና ፣ የኤዛቤላ ፣ መንግሥት ፣ ተነወረ ። ይህን ፣ ሕግ ፣ ያቆሙበት ፣ ምክንያት ፣ ሕዝባቸው ፣ ከካቶሊክ ፣ ሃይማኖት ፣ በቀር ፣ ሌላውን ፣ እንዳይቀበል ፣ ለመከልከል ፣ ነበር ።

፪ ፤ መናፍቅ ፣ ተብለው ፣ የተጠረጠሩትን ፣ ሰዎች ፣ ይዘው ፣ ቅዝቃዜ ፣ ወደ ፣ አለበት ፣ ወደ ፣ መጥፎ ፣ እስር ፣ ቤት ፣ ያገቡዋቸው ፣ ነበር ። ከዚህ ፣ ወዲያ ፣ ከላይ ፣ እስከታች ፣ ረጅም ፣ ቀሚስ ፣ ተጐናንበው ፣ በተቀመጡት ፣ መርማሪች ፣ ፊት ፣ ያቀርቡዋቸዋል ፤ ፊታቸው ፣ ተሸፍኖ ፣ አይታይም ። ነገር ፣ ግን ፣ እስረኞቹን ፣ እያሾለቁ ፣ የሚመለከቱበት ፣ በዐይናቸው ፣ ልክ ፣ ሁለት ፣ ቀዳዳዎች ፣ አሉዋቸው ።

፫ ፤ የተከሰሱት ፣ ሰዎች ፣ ስለ ፣ በደላቸው ፣ ይቅርታ ፣ ካላላመኑ ፣ በልዩ ፣ ልዩ ፣ ሥቃይ ፣ ይሣቀያሉ ። አንድ ፣ አንድ ፣ ጊዜም ፣ በቤት ፣ ጣራ ፣ ይሰቅሉዋቸውና ፣ ትንሽ ፣ ካቄዩአቸው ፣ በኋላ ፣ ገመዱን ፣ ሲለቁት ፣ ወደ ፣ መሬት ፣ ወርደው ፣ ሊሰባበሩ ፣ ሲደርሱ ፣ እንደ ፣ ገና ፣ ወደ ፣ ላይ ፣ ይስቡዋቸዋል ።

፬ ፤ እንዲህ ፣ በማድረግ ፣ ይጎዱዋቸውና ፣ እስረኞቹ ፣ ሁለመናቸው ፣ ተስፍሖው ፣ ተለያይቶ ፣ ውልቅልቅ ፣ ይላሉ ። እስረኛው ፣ ይህን ፣ ያህል ፣ ሥቃይ ፣ ተቀብሎ ፣ መርማሮች ፣ እንደሚፈልጉት ፣ ካላደረገ ፣ ፊቱን ፣ ስብ ፣ ነገር ፣ ይቀቡና ፣ ወደ ፣ እሳት ፣ ያቀርቡታል ። እንዲያው ፣ ባጭሩ ፣ የሚሠሩት ፣ የጭከና ፣ ሥራቸውን ፣ ለመናገር ፣ እጅግ ፣ የሚያስፈራ ፣ ነው ።

፭ ፤ መርማሮች ፣ እስረኞችን ፣ ብዙ ፣ ሥቃይ ፣ ካስቀበሉዋቸው ፣ በኋላ ፣ ደግሞ ፣ ሊያቃጥሉዋቸው ፣ ተሰናድተው ከዚህ ፣ ወዲያ ፣ የተፈረደባቸው ፣ ሰዎች ፣ የእሳት ፣ ነበልባል ፣ ሥዕል ፣ የተሳለበት ፣ ልብስ ፣ እንደ ፣ ለበሱ ፣ ይወጣሉ ። ደግሞም ፣ አባብና ፣ አውሬ ፣ እንደሚውጣቸው ፣ ሆኖ ፣ የተሣለበትን ፣ ልብስ ፣ ደረታቸውን ፣ ያለብሱዋቸዋል ።

፮ ፤ ወደሚቀመጡበት ፣ ስፍራ ፣ በደረሱ ፣ ጊዜ ፣ ተምሰሶ ፣ ጋር ፣ በሰንሰለት ፣ ያስሩዋቸውና ፣ ዝግ ፣ ብሎ ፣ በሚነድ ፣ እሳት ፣ እስኪሞቱ ፣ ድረስ ፣ ያሳርሩዋቸዋል ። ሕይወታቸው ፣ እስክትለይ ፣ ድረስ ፣ ሁለት ፣ ወይም ፣ ሦስት ፣ ሰዓት ፣ ያህል ፣ በሞት ፣

ፃዕር ፡ ይጨነቃሉ ። የሃይማት ፡ መርማሮች ፡ የተባሉት ፡ እንዳህ ፡ የሚያስፈሩ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ። እንዲህ ፡ የመሰለ ፡ ሥራ ፡ በኢጣልያና ፡ በሌሎችም ፡ የካቶሊክ ፡ አገሮች ፡ በተባሉት ፡ ሁሉ ፡ ገብቶ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ሲሠራበት ፡ ቈይቷል ። የሃይማኖት ፡ መርማሮች ፤ እስኪሻሩ ፡ ድረስ ፡ ሠላሳና ፡ አርባ ፡ ሺሕ ፡ ሰው ፡ ከነነፍሳቸው ፡ አቃጥለው ፡ ፈጅተዋል ።

፯ ፤ የሃይማኖት ፡ ምርመራን ፡ ስናስብ ፡ መቸውንም ፡ ይህ ፡ ሥራ ፡ የፌርዴናንድንና ፡ የኤዛቤላን ፡ መንግሥት ፡ አሳድፎትና ፡ ቀልሞት ፤ ነብዘት ፡ እናያለን ። የዚህ ፡ ንጉሥና ፡ የዚች ፡ ንግሥት ፡ ክብር ፡ ሆኖ ፡ የሚታየው ፡ አሜሪካን ፡ ለማግኘት ፡ በፈለገ ፡ ጊዜ ፡ ለክሪስቶፎር ፡ ኮሎምቡስ ፡ ገንዘብ ፡ መስጠታቸው ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ኮሎምቡስ ፡ አሜሪካን ፡ ስለ ፡ አገኘ ፡ ሽልማቱ ፡ እስራት ፡ ሆነ ።

፰ ፤ እስጳኞች ፡ ድል ፡ አግኝተው ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ ያገሩ ፡ ሀብት ፡ እንዲሁ ፡ ብዙ ፡ ነበርና ፡ ከሌላው ፡ ከአውሮጳ ፡ አገር ፡ ይልቅ ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ በእስጳንያ ፡ እጅግ ፡ ትሩፍ ፡ ሆነ ። ነገር ፡ ግን ፡ እስጳንያ ፡ ከአሜካ ፡ የቅኝ ፡ አገ ፎዋ ፡ እውነተኛ ፡ ጥቅም ፡ ማግኘትዋ ፡ ያጠራጥራል ። ባገራቸው ፡ ተቀምጠው ፡ መሬታቸውን ፡ በማረስ ፡ ፈንታ ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ለመፈለግ ፡ ብለው ፡ ባላገሮ ችዋ ፡ ውቅያኖስን ፡ ተሻግረው ፡ ሄዱ ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ የሃይማኖት ፡ ምርመራ ፡ ደንብ ፡ ያቆሙበት ፡ መቼ ፡ ነው ፡ ?
የዚህ ፡ አሳብ ፡ ምንድነው ፡ ? የተጠረጠረውን ፡ ሰው ፡ እንዴት ፡ ያደ ርጉት ፡ ነበር ፡ ?

፪—፫ ፤ የምርመራውን ፡ ሁኔታ ፡ ተናገር ። የተከሰሱትን ፡ ሰዎች ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ሥቃይ ፡ ያሰቀብሉዋቸው ፡ ነበር ፡ ?

፬—፮ ፤ በምርመራው ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ዘመን ፡ ሠሩበት ፡ ? የታሰሩትን ፡ እንዴት ፡ አድርገው ፡ ያቃጥሉዋቸው ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ ተናገር ።

፯ ፤ የፌርዴናንድና ፡ የኤዛቤላ ፡ መንግሥት ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
የመንግሥታቸው ፡ ክብር ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
የኮሎምቡስ ፡ ፍጻሜ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፰ ፤ እስጳኞች ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ? የእስጳኞች ፡ ሀብት ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
በአሜሪካ ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ ለእስጳኞች ፡ ጥቅም ፡ ሰጠ ፡ ወይ ፡ ?
ተጠቀሙበትን ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፪፹፩ ፡ ኤውሮጳ ።

### ስለማይሸነፉ ፡ መርከቦችና ፡ ስለ ፡ እስጳንያ ፡ ንጉሥ ፡ ሁኔታ ፡

### የዛሬው ፡ እስጳንያ ፡ ጉዳይ ።

፩ ፤ ከብዙዎች ፡ ኀያለኞች ፡ ነገሥታት ፡ አንዱ ፡ እጅግ ፡ ኀያለኛ ፡ ተብሎ ፡ የተጠራ ፡ ሁለተኛ ፡ ፊሊጵ ፡ የተባለው ፡ የእስጳንያ ፡ ንጉሥ ፡ ነው ። እርሱም ፡ በ፲፭፻፺ ዓ.ም.

በፖርቱጋልም ፡ ላይ ፡ ነገሠ ፡ እንጂ ፡ ንጉሥ ፡ መባሉ ፡ በእስጳንያ ፡ ብቻ ፡ አልነበረም ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ፖርቱጋል ፡ በኋላ ፡ ራስዋን ፡ ችላ ፡ ለብቻዋ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ የተለየች ፡ መንግሥት ፡ ሆነች ።

ባሥራ ፡ ሁለተኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ከእስጳንያ ፡ ነጻ ፡ ወጥታ ፡ በራስዋ ፡ አዳሪ ፡ መሆንዋን ፡ መጀመሪያ ፡ አስታውቃ ፡ ነበር ።

፲፯ ፤ ፊሊጵ ፡ እንግሊዝን ፡ እወጋለሁ ፡ ብሎ ፡ ይከጅል ፡ ነበርና ፤ ለዚሁ ፡ ብሎ ፡ ሰማኒያ ፡ የጦር ፡ መርከቦች ፡ አሰናዳ ። እነዚህም ፡ መርከቦች ፡ የማይሸነፉ ፡ አርማዳ ፡ ይባላሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ የእንግሊዝ ፡ መርከቦች ፡ እጅግ ፡ አድርገው ፡ አስጨነቋቸው ፡ እንዲያውም ፡ በመጨረሻው ፡ ሳይዋጉ ፡ ድል ፡ ሆነው ፡ ተሸነፉ ። (ማዕበሉ ፡) የባሕሩ ፡ ሞገድ ፡ እጅግ ፡ በርትቶ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ከነዚሁ ፡ አያሎቹን ፡ መርከቦች ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ ጠረፍ ፡ እየነዳ ፡ አስጠጋቸው ።

፲፰ ፤ የፊሊጵ ፡ ልጅ ፡ አእምሮ ፡ ያነሰው ፡ ሰው ፡ ነበር ። አሙዋሟቱም ፡ እጅግ ፡ የተለየ ፡ ነበር ፤ አንድ ፡ ቀን ፡ በምክር ፡ ቤት ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ ባጠገቡ ፡ ባንድ ፡ ትልቅ ፡ ምድጃ ፡ (እንክርት ፡) እሳት ፡ ይነድ ፡ ነበርና ፡ ሙቀቱ ፡ እጅግ ፡ ያስጨንቅ ፡ ነበር ።

፲፱ ፤ የተቀመጠበትን ፡ ወንበር ፡ ካለበት ፡ ፈቀቅ ፡ ለማድረግ ፡ ሰውዬው ፡ ግዙፍ ፡ ስለ ነበረ ፡ ነዲዱን ፡ እንዲያሳንሱለት ፡ አሽከሮቹን ፡ ጠራ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ሥራው ፡ እሳት ፡ መቆስቆስ ፡ የነበረው ፡ አሽከር ፡ በዚያ ፡ አልነበረም ። የቀሩትም ፡ አሽከሮች ፡ ሥራቸው ፡ ይህ ፡ አልነበረምና ፡ አላሰቡበትም ፡ ነበር ፤ ስለዚህ ፡ እሳቱ ፡ አብልጦ ፡ እየተንበለበለ ፡ ነደደና ፡ ንጉሡ ፡ ተልክ ፡ ያለፈ ፡ ሙቀት ፡ ስለ ፡ ተሰማው ፡ በዚሁ ፡ ጠንቅ ፡ ታሞ ፡ እንደ ፡ ሌላ ፡ ሳይሆን ፡ በእስጳንያ ፡ ንጉሥነት ፡ ስም ፡ ሞተ ።

፳ ፤ በሺ ፡ ፯፻ ፡ ዓ. ም. ቻርልስ ፡ ሁለተኛ ፡ የእስጳንያው ፡ ልጆች ፡ ሳይወልድ ፡ ሞተ ። የሉዊስ ፡ ዐሥራ ፡ አራተኛ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ የአንጆ ፡ ዱክ ፡ የተባለ ፡ የፈረንሳይ ፡ ጐልማሳ ፡ ፕሪንስ ፡ ፊሊጵ ፡ በዙፋኑ ፡ ተቀመጠ ። የዚህም ፡ ቤት ፡ ሰቦች ፡ የእስጳንያ ፡ ቡርቦንስ ፡ ይባላሉ ።

፳፩ ፤ ይህም ፡ ሁኔታ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በኤውሮጳ ፡ ጦርነትን ፡ አስነሣ ። የኦስትሪያ ፡ አርችዱክ ፡ ቻርልስ ፡ የእስጳንያን ፡ ዘውድ ፡ ተመኝቶ ፡ ነበርና ፡ እጁን ፡ ጫነበት ። እርሱና ፡ የአንጆ ፡ ፊሊጵ ፡ እየተዋጉ ፡ በየተራ ፡ ተከተማው ፤ ተማድሪድ ፡ ሲወጡ ፡ ሲገቡ ፡ በመጨረሻው ፡ ዘውዱን ፡ ፊሊጵ ፡ እንደያዘ ፡ ቀረ ።

፳፪ ፤ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እስጳንያ ፡ ተእንግሊዝ ፡ ጋር ፡ ስትዋጋ ፡ ኑራለች ። በአሜሪካን ፡ ዐመፅ ፡ ጊዜ ፡ ተፈረንሳይ ፡ ጋር ፡ ሁና ፡ ትወጋት ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በሺ ፡ ፯፻ ፹፫ ፡ ዓ. ም. ነገሩ ፡ በዕርቅ ፡ ተጨረሰ ። ደግሞ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ቈይቶ ፡ በእንግሊዝና ፡ በፈረንሳይ ፡ መኻከል ፡ ሌላ ፡ ጦርነት ፡ ተነሣ ። በዚህም ፡ እስጳንያ ፡ ከጦርነቱ ፡ ለመግባት ፡ ግድ ፡ ሆነባት ።

፳፫ ፤ በሺ ፡ ፰፻—፰ ዓ. ም. አንደኛ ፡ ናፖሊዎን ፡ እጅግ ፡ አድርጎ ፡ ኀይል ፡ ስለ ፡ ተሰማው ፡ የእስጳንያን ፡ ንጉሥ ፡ ዙፋኑን ፡ እንዲለቅ ፡ አስገደደው ።

ይህም ፡ ንጉሥ ፡ ፌርዲናንድ ፡ ሰባተኛ ፡ ይባል ፡ ነበር ፤ ናፖሊዮንም ፡ የእስጳን ያን ፡ ዘውድ ፡ ወሰደና ፡ በወንድሙ ፡ በዮሴፍ ፡ ቦናፓርቴ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ጫነው ።

፱ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የሚበዙት ፡ እስጳኞች ፡ ንጉሥነቱን ፡ አላጸደቁለትም ። እንደ ፡ ንጉሣችን ፡ አድርገን ፡ አንቀበለውም ፡ ብለው ፡ አሻፈረን ፡ አሉ ። ከዚህ ፡ ወዲያ ፡ ጦርነት ፡ ተነሣ ። የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ በእስጳንያና ፡ በፖርቱጋል ፡ ላይ ፡ ጦር ፡ ሰደደ ። የዌሌንግተን ፡ ዱክ ፡ መጀመሪያ ፡ ፈረንሳይን ፡ ድል ፡ ያደረገ ፡ ከዚያ ፡ ነው ።

፲ ፤ የቀድሞው ፡ የእስጳንያ ፡ ንጉሥ ፡ ፌርዲናንድ ፡ ተመልሶ ፡ በዙፋኑ ፡ የተተካው ፡ ባንድ ፡ ሺ ፡ ፰፻፲፬ ዓ. ም. ነው ። በሺ ፡ ፰፻፴፫ ዓ. ም. ሞተና ፡ ከተወለደች ፡ ፫ ፡ ዓመት ፡ የሆናት ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ነበረችውና ፡ ኤዛቤላ ፡ ሁለተኛ ፡ ተብላ ፡ ንግሥት ፡ ሆነች ።

፲፩ ፤ ይህ ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ በፌርዲናንድ ፡ ወንድም ፡ በዶን ፡ ካርሎና ፡ በሕፃኒቱ ፡ ንግሥት ፡ ንግሥት ፡ በሚሪያ ፡ ኤዛቤላ ፡ መኻከል ፡ ጸብ ፡ ተነሣና ፡ እስከ ፡ ፩ሺ ፡ ፰፻፷፰ ፡ ዓ. ም. ድረስ ፡ በእስጳንያ ፡ ሁከትና ፡ ድብልቅልቅ ፤ ሽብርና ፡ ዘረፋ ፡ ሆነ ። ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ተከራካሪ ፡ ጉባኤ ፡ ተነሣና ፡ እስጳንያ ፡ ታወከች ። ንግሥት ፡ ኤዛቤላ ፡ መስከረም ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ሺ ፡ ፰፻፷፰ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ከእስጳንያ ፡ ሸሸች ። ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ አገሩ ፡ በማኅበር ፡ ተገዛ ፤ እነርሱም ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ማርሻል ፡ ሲራኖ ፡ በንጉሥ ፡ ፈንታ ፤ ጄኔራል ፡ ፒሪም ፡ የሚኒስቴሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዴንት ፡ ሆኑ ።

፲፪ ፤ የሁከቱ ፡ ዘመን ፡ አለፈና ፡ እነዚህ ፡ ስለ ፡ ዋናው ፡ ፍርድ ፡ ሸንጎ ፡ ብዙ ፡ ከተ ጋደሉ ፡ በኋላ ፡ ጄኔራል ፡ ፒሪምን ፡ ዋና ፡ አድርገው ፡ የሕዝቡ ፡ ምርጫ ፡ በኢ ጣሊያው ፡ ንጉሥ ፡ በቪክቶር ፡ አማኑኤል ፡ በሁለተኛው ፡ ልጁ ፡ ላይ ፡ ወደቀና ፡ በሺ ፡ ፰፻፸ ዓ. ም. ቀዳማዊ ፡ አሜዶ ፡ ተብሎ ፡ ነገሠ ። ይህም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሥ ፡ ሆኖ ፡ አልቈየም ። በየካቲት ፡ ሺ ፡ ፰፻፸፫ ዓ. ም. ከመንግሥቱ ፡ ተሻረ ። ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ እስጳንያ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በሬፑብሊክ ፡ ተገዛ ። በጥር ፡ ሺ ፡ ፰፻፸፭ ዓ. ም. አልፎንሶ ፡ ፲፪ኛ ፡ የንግሥት ፡ ኤዛቤላ ፡ ልጅ ፡ በእስጳንያ ፡ ዙፋን ፡ ተቀመጠ ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ ፊሊጵ ፡ ሁለተኛ ፡ የተባለው ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ፖርቱጋል ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ?

፪ ፤ (ኢንቢሲብል ፡ ) አርማዳ ፡ የማይሸነፍ ፡ መርከብ ፡ የሚሉት ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? የሁለተኛ ፡ ፊሊጵን ፡ ልጅ ፡ ሞት ፡ ተናገር ።

፫ ፤ በሺ ፡ ፯፻ ዓ. ም. ምን ፡ ሆነ ፡ ? የቻርልስን ፡ ሁለተኛ ፡ ዙፋን ፡ ማን ፡ ወረሰ ፡ ? የእስጳንያ ፡ ቡርቦንስ ፡ የተባሉ ፡ እነማናቸው ፡ ?

፬ ፤ ቻርልስና ፡ ፊሊጵ ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ ለምን ፡ ሄዱ ፡ ? የትኛው ፡ ድል ፡ አደረገ ፡ ?

፭ ፤ እስጳንያ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ?

፮ ፤ በ፩ሺ ፡ ፰፻፰ ፡ ዓ. ም. ናፖሊዮን ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ? ፌርዲናንድ ፡ ፯ኛ ፡ የተ ባለ ፡ ማነው ? ።

ናፖሊዎን ፡ በእስጳንያ ፡ ማንን ፡ አነገሠ ፡ ?

፱ ፤ እስጳንያዎች ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ? የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ? ሎርድ ፡ ዌልንግቶን ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ?

፲ ፤ ፌርዲናንድ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ መንግሥቱ ፡ ተመለሰ ፡ ? ዙፋኑን ፡ ማን ፡ ወረሰ ፡ ? ንግሥት ፡ ኤዛቤላ ፡ ከእስጳኝ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ሸሸች ፡ ?

፲፩ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ምን ፡ ሆነ ፡ ? የእስጳንያ ፡ ንጉሥ ፡ ለመሆን ፡ ማን ፡ ተመረጠ ፡ ? ያሁኑ ፡ መንግሥት ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?